# የከተማ ፡ ውስጥ ፡ ችግሬ ።

ትምህርቴን ፡ ትቼ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ እያልኩ ፡ ያለ ፡ ሥራና ፡ ያለ ፡ ድጋፍ ፡ ኑሮዬን ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ለማሳለፍ ፡ ባሰብኩት ፡ ዓይነት ፡ ሊሳካልኝ ፡ አልቻለም ። ላይ ፡ ታች ፡ ብዬ ፡ የዕለት ፡ ጉርሴን ፡ የማላጣ ፡ መስሎኝ ፡ የነበረው ፡ ሳይሠሩ ፡ መብላት ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ተረዳሁ ፤ በየሆቴሉ ፡ የማየው ፡ እንጀራና ፡ ወጥ ፡ ከሽታው ፡ በቀር ፡ ሌላው ፡ ሳንቲምን ፡ የሚጠይቅ ፡ ሆነ ። የማየው ፡ የምግብ ፡ ዓይነት ፡ ምራቄን ፡ እንድውጥ ፡ ከንፈሮቼን ፡ በመላሴ ፡ እንዳለሰልስ ፡ ይረዳኝ ፡ ነበር ። ግራ ፡ ሲገባኝና ፡ ረሃብ ፡ ውስጥ ፡ ውስጤን ፡ በልቶኝ ፡ መቆም ፡ ሲያቅተኝ ፡ ለምኜ ፡ ለመ ብላት ፡ ቁርጥ ፡ አሳብ ፡ አደረግሁና ፡ የእኔ ፡ ብጤዎች ፡ አጠገብ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ የባላትን ፡ ስምና ፡ የሚውሉበትን ፡ ቀን ፡ አጥንቼ ፡ እንደነሱ ፡ አንዱን ፡ ሥፍራ ፡ ብይዝ ፡ መኖር ፡ እንደምችል ፡ እምነቴ ፡ ገፋፋኝ ። ላንድ ፡ ወር ፡ በሙሉ ፡ በወሰድኩት ፡ ጥናት ።

ባንድ ፣ ልደታ—በሁለት ፣ ታድዮስና ፡ አባ ፡ ጉባ—ሦስት ፣ በዓታ— በአራት ፣ ዮሐንስ ፡ ሐዋርያ—(ወልደ ፡ ነጐድጓድ ፡) በአምስት ፣ አቡነ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ—ስድስት ፣ ኢየሱስ—ሰባት ፣ ሥላሴ—ስምንት ፣ አባ ፡ ኪሮስ—ዘጠኝ ፣ ሰለስቱ ፡ ምዕት—አሥር ፣ መስቀለ ፡ ኢየሱስ—አሥራ ፡ አንድ ፣ ሐና ፡ ማርያም—አሥራ ፡ ሁለት ፣ ሚካኤል—አሥራ ፡ ሦስት ፣ እግዚአብሔር ፡ አብና ፡ ሩፋ ኤል—አሥራ ፡ አራት ፣ አቡነ ፡ አረጋዊ—አሥራ ፡ አምስት ፣ ቂር ቆስ—አሥራ ፡ ስድስት ፣ ኪዳነ ፡ ምሕረት—አሥራ ፡ ሰባት ፣ እስ ጢፋኖስ—አሥራ ፡ ስምንት ፣ ዘካርያስ—አሥራ ፡ ዘጠኝ ፣ ገብር ኤል—ሃያ ፣ ሕንጸተ ፡ ቤታ ፡ ለማርያም—ሃያ ፡ አንድ ፣ ማርያም— ሃያ ፡ ሁለት ፣ ሉቃስ ፡ ወንጌላዊ—ሃያ ፡ ሦስት ፣ ጊዮርጊስ—ሃያ ፡ አራት ፣ ተክለ ፡ ሃይማኖት—ሃያ ፡ አምስት ፣ መርቆርዮስ—ሃያ ፡ ስድስት ፣ ቶማስ ፡ ሐዋርያው—ሃያ ፡ ሰባት ፣ መድኃኔ ፡ ዓለም— ሃያ ፡ ስምንት ፣ አማኑኤል—ሃያ ፡ ሰጠኝ ፣ ባለወልድ—(ባለ ፡ እግ

ግዚአብሔር ፡ ) ሠላሳ ፡ ማርቆስ ፡ ሐዋርያ—መሆናቸውን ፡ በቃሌ፡
ምጥጥ ፡ አድርጌ ፡ ከሰውነቴ ፡ ጋር ፡ አዋሃድኳቸው ።

በየትኛው ፡ በዓል ፡ ልመና ፡ እንደምጀምር ፡ መረጣ ፡
ውስጥ ፡ ገባሁና ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ሊመላለስ ፡ በሚችልበት ፡ በእ
ሁድ ፡ ቀን ፡ ለመጀመር ፡ ወሰንኩ ፤ እንዳጋጣሚ ፡ እኔ ፡ የመረጥ
ኩት ፡ እሑድ ፡ ወር ፡ በገባ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ስለነበረ ፡ ከበ
ዓታ ፡ ጋር ፡ ድርብ ፡ ሰንበት ፡ ነበር ። « ታዲያ ፡ ስለድርብ ፡ ሰን
በት ፡ ብዬ ፡ ልለምን ፡ ነውን ? ስለበዓታ ፡ ብቻ ፡ ብልስ ፡ ሰንበቱ፡
በበኩሉ ፡ አይቀየመኝምን ? ሰውስ ፡ ምን ፡ ይለኛ ፡ ተሳስቼ ፡
ስም ፡ ስጠራ ፡ የሰማ ፡ እንደሆነ ? የትኛውን ፡ ስም ፡ ጠርቼ ፡
ልለምን ፡ » እያልኩ ፡ በዚቹ ፡ ደግሞ ፡ ስጨነቅ ፡ አደርኩና ፡
ጠዋት ፡ ገና ፡ የወፍቹ ፡ ጭውታ ፡ ሳይሰማ ፡ ተቀምጬ ፡ የምለም
ንበትን ፡ ሥፍራ ፡ ሰው ፡ ሳያየኝ ፡ ለማማረጥ ፡ ካደርኩበት ፡
ወጥቼ ፡ ስሄድ ፡ ቄሱና ፡ መነኩሴው ፡ እንደዚሁም ፡ ሕዝቡ ፡
ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲጓዝ ፡ ለማኙ ፡ ሁሉ ፡ ሥፍራ ፡ ሥፍ
ራውን ፡ ይዞ ፡ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ ለማኝ ፡ እበልጥ ፡ አሳዝናለሁ ፡
በሚልበት ፡ በአለማመን ፡ ቄንጥና ፡ ፈሊጥ ፡ እየተጠቀመ ፡ «ስለ ፡
ሰንበት ፡ » ሲል ፡ አየሁ ። በዕለቱ ፡ « ስለ ፡ ሰንበት » እያልኩ ፡
መለመን ፡ እንዳለብኝ ፡ ተረድቼ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የአባባ
ልም ፡ ዘዴ ፡ አለውና ፡ ትንሽ ፡ ልምድ ፡ ያስፈልገዋል ። ሙከ
ራውን ፡ ሳሰላስል ፡ አምልጦኝ ፡ የጅብ ፡ ጕሽምታ ፡ በመሰለ ፡
ድምፅ ፡ « ስለ ፡ ሰንበት ! » ስል ፡ አካባቢው ፡ ከነበሩት ፡
የእኔ ፡ ብጤዎች ፡ ሦስቱ ፡ ሰሙኝ ። እኔም ፡ ደንግጬ ፡ ፊት ፡
ፊታቸውን ፡ በፍርሃትና ፡ በፈገግታ ፡ ብመለከት ፡ « አፌዝክ
ብን ! እኛ ፡ ስለቸገረን ፡ ብንለምን ፡ » ብለው ፡ አይወርዱብኝም !
አንዱ ፡ ተቀብሎ ፡ ላንዱ ! አንደኛው ፡ በያዘው ፡ ቆመጥ ፡ ወግሮ ፡
ለሌላው ፡ ሲያቀባብሉኝና ፡ ሲቀባበሉኝ ፡ ያለሁበትን ፡ ሥፍራ ፡
እስከመሳት ፡ አደረሱኝና ፡ ከነበርኩበት ፡ ሥፍራ ፡ አባረሩኝ ።
ራቅ ፡ ብዬ ፡ በመቀመጥ ፡ ጥቂት ፡ ካረፍኩ ፡ በኋላ ፡ የልመናው ፡



ሥራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያልፈቀደው ፡ መሆኑን ፡ ተረድቼ ፡
ልመናውን ፡ በመተው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሔድኩና ፡
«እግዚኦ ፡ መሐረነ ፡ ክርስቶስ ፡ » እል ፡ ጀመር ። በደረሰብኝ ፡
ቅጥቀጣ ፡ መቆም ፡ አቅቶኝ ፡ ስነሳና ፡ ስወድቅ ፡ ሥርዓተ ፡ ቅዳ
ሴው ፡ ተፈጽሞ ፡ ካህናቱ ፡ ጸሎት ፡ እንዲደረግ ፡ ካዘዙ ፡ በኋላ ፡
« መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ባወቀው ፡ ሰይጣን ፡ በሰወረው ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ይፍታ ፡ » ሲሉ ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡
« ይፍቱኝ ! ይፍቱኝ ፡ » ብሎ ፡ አጉረምርሞ ፡ ተነሣ ። እኔም ፡
«እንዴት ፡ ነው ! መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያወቀውን ፡ ሰይጣን ፡ የሚሰ
ውረው ? አንዱ ፡ አውቆ ፡ አንደኛው ፡ የሰወረውን ፡ ነው ፡ እግዚ
አብሔር ፡ የሚፈታው ? ኧረ ፡ እንዴት ፡ ነው ? ሰይጣን ፡ ከመን
ፈስ ፡ ቅዱስና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ የሚጠራው ?
የመሰወር ፡ ኃይል ፡ ያለው ፡ ሰይጣን ፡ ጥበቡ ፡ ምን ፡ ያህል ፡
ትልቅ ፡ ይሆን ? » እያልኩ ፡ በመገረም ፡ ከእኔ ፡ ብጤዎች ፡ የደረ
ሰብኝን ፡ ኃይለኛ ፡ ቅጥቀጣ ፡ ለመርሳት ፡ ሞከርኩ ።

ሕዝቡ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ቅጠር ፡ ግቢ ፡ እንደወጣ ፡
አንድ ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ከየአጥቢያው ፡ የመጣውን ፡
ዳቦና ፡ ቆሎ ፡ እንዲሁም ፡ ጠላ ፡ ተከፋፍሎ ፡ ሲበላ ፡ ለኔም ፡
አንድ ፡ ቁራሽ ፡ ዳቦ ፡ አንዲት ፡ ጭብጥ ፡ ቆሎና ፡ አንድ ፡ ኩባያ ፡
ጠላ ፡ ተሰጥቶኝ ፡ በእውነቱ ፡ ሆዴን ፡ በመጠኑ ፡ ሞላሁት ። የሰ
ውን ፡ እጅ ፡ አይቼ ፡ ለእራት ፡ ወይም ፡ ለምሳ ፡ አገኘው ፡ ከነበ
ረው ፡ ቁራሽ ፡ በጣም ፡ የበለጠ ፡ ነበርና ፡ የዕለቱ ፡ ልመና ፡
ተደናቅፎብኝ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሔዴ ፡ በጣም ፡
አስደሰተኝ ፤ ግን ፡ እሁድ ፡ የሚመጣው ፡ በየሳምንቱ ፡ እንጂ ፡
በየቀኑ ፡ ባለመሆኑ ፡ በተጠቀሱትም ፡ ሌሎች ፡ ባላት ፡ እንደ
እሁድ ፡ ሊቃና ፡ ስለማይችል ፡ ዳቦ ፡ ጠላ ፡ ቆሎ ፡ ስለማይገኝ ፤
የሆዴ ፡ ችግር ፡ ሊቃለል ፡ አልቻለም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በቃሌ ፡
ባጠናኋቸው ፡ የበዓላት ፡ ስም ፡ ተጠቅሜ ፡ ወደ ፡ ልመና ፡ መሔ
ዱን ፡ ለጊዜው ፡ ተውኩ ። «ጥቅም ፡ ሳትሰጥ ፡ ሰው ፡ በደከመበ
ትና ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ባበቀለው ፡ አበባ ፡ ክንፎችዋን ፡ ዘርግታና፡

ላይን ፡ ብቻ ፡ አምራ ፡ ሳትሠራ ፡ እንደምትበላው ፡ ቢራ ፡ ቢሮ ፡ (ብራብሮ) ፡ ሙሉ ፡ ሰውነት ፡ እያለኝ ፥ ዓይኖቼ ፡ እያዩ ፥ እጅ ፡ እግሬ ፡ ሳይሰናከል ፥ ጠቅላላው ፡ ጤናዬ ፡ ሳይታወክ ፥ እንዴት ፡ በየቦታው ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እየጠራሁ ፡ ሰው ፡ በድካሙ ያፈራውን ፡ ገንዘብ ፡ አታልዬ ፡ እቀበላለሁ ? » እያልኩ ፡ ራሴን ፡ በራሴ ፡ እጠይቅና ፡ « እንዴ ፡ ኋላ ፡ ዓይኖቼ ፡ እያዩ ፡ በረሃብ ፡ ልሙት ?» ብዬ ፡ ጥያቄዬን ፡ በጥያቄ ፡ እመልሳለሁ ። ጥያቄዬ ፡ ጥያቄን ፡ ወልዶ ፡ በተገኘው ፡ መልስ ፡ የልመና ፡ ዝንባሌዬ ፡ ጨርሶ ፡ እንዲጠፋና ፡ ወደ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ተጠግቼ ፡ የዲቁና ፡ ትምህርት ፡ እንዳጠና ፡ ተወሰንኩ ።

ቁጭ ፡ ብዬ ፡ እያለሁ ፡ በአሳብ ፡ ብዙ ፡ ተጉዤ ፥ በአሳብ ፡ በመጓዜ ፡ በጣም ፡ ደክሞኝ ፥ ትንፋሼ ፡ ሁሉ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ ብሎ ! አልቦኝ ፥ « እፎይ ! እፎይ ! » ካልኩ ፡ በኋላ ፡ « ብድግ ፡ ልበልና ፡ የዛሬው ፡ የሆዴን ፡ ችግር ፡ ሊያቃልልኝ ፡ ወደቻለው ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ሄጄ ፡ ጠዋት ፡ ሲሰብኩ ፡ ድምፃቸው ፡ ያምር ፡ ለነበሩት ፡ ቄስ ፡ ገኩጓም ፡ መጣሁ ፥ የሊቀ ፡ ጠበብት ፡ ወልደ ሃና ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ የሙጥኝ ፡ ልበል ፡ » ብዬ ፡ ጉዞዬን ፡ ቀጠልኩ ። እዚያም ፡ እንደደረስኩ ፡ የጠዋቱ ፡ ሰባኪ ፡ አባ ፡ ሰብስቤ ፡ እንደሚባሉና ፡ የደብሩም ፡ አላፊ ፡ እርሳቸው ፡ መሆ ናቸውን ፡ ተረዳሁ ። ወዳሉበት ፡ ሄጄ ፡ ለጥ ፡ ብዬ ፡ እጅ ፡ ነሳሁ ። « እንዴት ፡ አደርክ ! » ብለው ፡ መስቀል ፡ አሳለሙኝና ፡ « ከወ ዴት ፡ መጣህ ፡ ወዳጄ ? » አሉኝ ፤ እኔም ፡ በተዘጋጀሁበት ፡ ጥናት ፡ በመጠቀም ፡ « ከጐጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ መጣሁ ፥ የሊቀ ፡ ጠበብት ፡ ወልደሃና ፡ ልጅ ፡ ነኝ » ስል ፡ መለስኩላቸው ። አባ ፡ የሊቀ ፡ ጠበብት ፡ ልጅ ፡ በመሆኔ ፡ ያስጠጉኛል ፡ ብዬ ፡ በልጅ ፡ አስተሳሰብ ፡ የወሰድኩት ፡ ግምት ፡ ትክክል ፡ ሊሆን ፡ አልቻለም ። ጉስቁልናዬን ፡ አይተው ፡ እኔን ፡ ከምንም ፡ ባለመቁ ጠር ፡ «እኛም ፡ ሊቀ ፡ ጠበብት ፡ አልተባልን ፡» ብለው ፡ የውሸት ፡ አባቴን ፡ ካሸሚጠጡ ፡ በኋላ ፡ «ውዳሴ ፡ ማርያምን ፡ ታውቃለህ »፡ ሲሉ ፡ ጠየቁኝ ። እኔም ፡ ድንግርግር ፡ አለኝና ፡ « አባቴ ፡ ታሪክና ፡



ምሳሌን ፡ አጣርቼ ፡ አውቃለሁ ፥ ውዳሴ ፡ ማርያም ፡ ከዚህ ፡ ይከ ብዳል ? » እንዳልኳቸው ፡ የኔ ፡ ታሪክና ፡ ምሳሌ ፡ መጽሐፍ ፡ ሳይ ሆን ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ተረትና ፡ እንቆቅልሽ ፡ ወስደውብኝ ፡ ፊታ ቸውን ፡ ጠቆርቆር ፡ አደረጉብኝ ። ለጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ ከእግር ፡ እስከራሴ ፡ ከተመለከቱኝ ፡ በኋላ ፡ « በል ፡ ልጄ ፡ እዚህም ፡ ያለው ፡ ተማሪ ፡ አልቻልነውምና ፡ ወደ ፡ መጣህበት ፡ ተመለስ ፡» አሉኝ ፡ በቁጣ ፡ ቃል ። የአባ ፡ ቁጣ ፡ ከነበረብኝ ፡ የችግር ፡ ቁጣ ፡ ጋር ፡ ሳመዛዝነው ፡ አነስተኛ ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘሁት ፡ « ታሪክና ፡ ምሳሌ ፡ ያልኮት ፡ እኮ ፡ መንግሥት ፡ በየትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የሚ ሠራበትን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፡ አባቴ ፡ » አልኳቸው ፡ በጣም ፡ በለዘበ ፡ ቃል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቁጣቸው ፡ ጥቂት ፡ እየበ ረደ ፡ የሔደ ፡ መሰለ ። በል ፡ እስኪተመላልስህ ፡ ጠይቅ ፡ ከማለታ ቸውም ፡ ሌላ ፡ እስከዚያው ፡ ድረስ ፡ ጠዋት ፡ ጠዋት ፡ ወደ ፡ ገዳሙ ፡ እየሄድኩ ፡ አንዳንድ ፡ ጭልፋ ፡ የባቄላ ፡ ንፍሮ ፡ እንድ ቀበል ፡ አዘዙልኝ ። በንፍሮው ፡ በኩል ፡ የተደረገልኝን ፡ እር ዳታ ፡ በማመስገን ፡ ለጥ ፡ ብዬ ፡ እጅ ፡ ነሳሁና ፡ መስቀላቸውን ፡ ተሳልሜ ፡ ተመለስኩ ።

«እንግዲህ ፡ በየቀኑ ፡ አንዳንድ ፡ ጭልፋ ፡ ንፍሮ ፡ አግኝቼ ፡ በዚህ ፡ ሕይወቴን ፡ መጠበቅ ፡ እችላለሁ ? ዘለዓለም ፡ በረንዳ ፡ ላይ ፡ ተኝቼ ፡ ለበረንዳው ፡ ንጣፍ ፡ ልብስ ፡ ሆኜ ፡ ልኖር ፡ ነው ን ? ለገላዬ ፡ ጨርቅ ፡ ያስፈልገኝ ፡ የለምን ? ታዲያሳ ? ምን ፡ ማድ ረግ ፡ ይገባኛል ? » እያልኩ ፡ አፌን ፡ ከፍቼ ፥ እንዴት ፡ የሕዝብ ፡ መናፈሻ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ዝንቡ ፡ እንደ ፡ ቀፎው ፡ ይመላለስብኝ ፡ ጀመር ። ወጭ ፡ ወራጁን ፡ እየተመለከ ትኩ ፡ ልቤ ፡ እንደ ፡ መሰወር ፡ አለና ፡ የተቀመጥኩበትን ፡ አካ ባቢ ፡ ወደ ፡ መጠርጠሩ ፡ ገባሁ ። ዙሪያዬን ፡ እየተመለከትኩ ፡ «ይህ ፡ ሥፍራ ፡ ገነት ፡ መሆን ፡ አለበት ፥ እኔም ፡ እንደ ፡ አባትና ፡ እናቴ ፡ ሞቼ ፡ አሁን ፡ ያለሁት ፡ ገነት ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ለካስ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሆኜ ፡ በረሃብ ፡ የምሰቃይ ፡ የሚመስለኝ ፥ በሕልሜ ፡ ነው ? ዛሬም ፡ ያየኋቸው ፡ ቄስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መላክ ፡ መንግሥት፡

ሰማያት ፡ ውስጥ ፡ ቀለብ ፡ ሲያዙልኝ ፡ ነው ! » እያልኩ ፡ በውኔ፡ እቃዥ ፡ ጀመር ። በኋላም ፡ ያለሁት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ ይሁን ፡ በምድር ፡ ገጽ ፡ በረሃብ ፡ መንገብገቤ ፡ ካልቀረ ፡ ምና ልባት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ የሚራቡበት ፡ ሥፍራ ፡ ከሆነ ፤ ምናምን ፡ ሠራርቼ ፡ ሆዴን ፡ ልሙላ ፡ በማለት ፡ አሽከርነት ፡ ወይም ፡ ዘበኝነት ፡ ለመቀጠር ፡ በየሥፍራው ፡ መዞር ፡ ጀመርኩ ። ግን ፡ አልሆነም ። ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እድሜዬም ፡ አሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ሆነኝ ። በሥራ ፡ ፈትነት ፡ ለመከሰስ ፡ በወንጀል ፡ ለመቀጣት ፡ ለአሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ እድሜ ፡ ተቀራርቤአለሁ ።

«እንደዚህ ፡ ለመንከራተት ፡ ለምን ፡ ተፈጠርኩ ? ወይስ ፡ ጭራሽ ፡ ሳልፈጠር ፡ በአሳብ ፡ የተፈጠርኩ ፡ በአሳብም ፡ የምንከራተት ፡ እንዲያው ፡ የሌለሁ ፡ ነገር ፡ እሆን ? ወይስ ፡ በእውነትም ፡ ወንድይፍራው ፡ ይባል ፡ የነበረ ፡ አባትና ፡ የዓይኔ ፡ አበባ ፡ ትባል ፡ የነበረችው ፡ እናት ፡ ወልደውኝ ፡ በየቀኑ ፡ እንደሚሰማኝ ፡ አባቴ ፡ በጦር ፡ሜዳ ፡ እናቴ ፡ በበሽታ ፡ ተሰቃይታ ፡ ሁለቱም ፡ አፈር ፡ ሆነው ፡ ቀርተው ፡ እኔ ፡ ረዳት ፡ በማጣቴ ፡ እንደዚህ ፡ እሰቃያለሁ ? ወይስ ፡ አባትና ፡ እናቴ ፡ ሳይሞቱ ፡ እኔም ፡ ያለችግር ፡ እያደግሁ ፡ የአሁኑ ፡ ችግሬ ፡ በሕልም ፡ ነው ? አንዲት ፡ ለሊት ፡ አባትና ፡ እናቴ ፡ መጥተው ፡ እኔ ፡ በተከራየሁት ፡ በአማረው ፡ ቤቴ ፡ ውስጥ ፡ አብረን ፡ እንደነበርን ፡ አስታውሳለሁ ፤ ይህስ ፡ ምን ፡ ሆነ ? አሁን ፡ የምጨነቀው ፡ በሕልም ፡ ይሆን ? ሣርና ፡ ቅጠሉ ፡ ወጭው ፡ ወራጁ ! መኪናው ፡ ጋሪው ፡ ይኸው ፡ ይታዩኛል ። እንደዚህ ፡ የተስተካከለ ፡ ነገር ፡ በሕልሜ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። የለም ! አባትና ፡ እናቴ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ መጥተው ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ እነሱን ፡ በሚገባ ፡ አይቼ ፡ ተቀመጡ ፡ ብዬ ፡ እንደዚሁ ፡ በተስተካከለ ፡ ሁኔታ ፡ አየኋቸው ። እህ ! አይደለም ፡ አሁን ፡ የማያቸው ፡ ነገሮች ፡ ጋሪው ፡ ሲያሳፍርና ፡ ሲሮጥም ፡ ድምፁ ፡ የሚሰማ ፡ መኪናውም ፡ ሲጮህ ፡ እኔን ፡ ጸጥታ ፡ የነሳኝ ፡ ወጭ ፡ ወራጁም ፡ ሲነጋገር ፡ የምሰማ ፡ ስለሆነ ፡ ከዚያን ፡ ዕለቱ ፡ ሁናቴ ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰል ፡ አይደለም ። አባ



ትና ፡ እናቴ ፡ ሲነጋገሩ ፡ ከንፈሮቻቸው ፡ ሲነቃነቅ ፡ እንጂ ፡ የሚሉትን ፡ መስማት ፡ አልችልም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ የእነሱ ፡ በእርግጥም ፡ ሕልም ፡ ሲሆን ፡ የዛሬው ፡ በውኔ ፡ የማልመው ፡ ቅዠት ፡ ነው ፡ » በሚል ፡ ደመደምኩ ።

## ው ሳ ኔ ።

«ዛሬ ፡ ፍንክች ፡ በምትባል ፡ ከተማ ፡ ፀሐይዋ ፡ ልትጠልቅ ፡ በኔ ፡ ግምት ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ሲቀራት ፡ ተነስቼ ፡ ስቆም ፡ የጥላዬ ፡ እርዝመት ፡ ዘጠኝ ፡ ጫማ ፡ ሆኖ ፤ ጊዜው ፡ የበጋ ፡ ወራት ፡ የካቲት ፡ ዘጠኝ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እሑድ ፡ ዕለት ፡ በዘመነ ፡ ማርቆስ ፡ እኔ ፡ የምናገረው ፡ በሕልሜ ፡ ሳይሆን ፡ በውኔ ፡ የተራብኩትና ፡ የተጠማሁትም ፡ በውኔ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ የሌሉኝ ፡ አባቴ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ሞቶ ፡ እናቴም ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ በችግር ፡ ከተሰቃየች ፡ በኋላ ፡ በበሽታ ፡ የሞተችና ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ረዳት ፡ የቀረሁ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የአሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ወጣት፡ መሆኔን ፡ አውቄ ፡ ወስኛለሁ ። ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ውሳኔዬን ፡ አልለውጥም ፡ በውኔ ፡ እያለሁ ፡ በሕልሜ ፡ ነው ፡ እያልኩ ፡ ራሴን ፡ በራሴ ፡ አላታልልም ። አንች ፡ የተቀመጥኩብሽ ፡ የፍንክች ፡ ከተማ ! አንች ፡ በአበባ ፡ ያጌጥሽና ፡ ልምላሜሽ ፡ ያማረ ፡ ውብ ፡ ሥፍራ ፡ አንተ ፡ በኃይል ፡ ከፍ ፡ ብለህ ፡ የተጣራውን ፡ አየር ፡ ያለሽምያ ፡ የምትመገብ ፡ ትልቅ ፡ ዛፍ ፡ በጥላህም ፡ የተጠቀምኩብህ ፡ ፍሬአማ ፡ ዛፍ ፡ የፀሐይን ብርሃን ፡ ስታጣ ፡ አንገትዋን ፡ ወደታች ፡ እንደምትቀለብሰዋ ፡ የሱፍ ፡ አበባ ፡ አንገትህን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ቀልብሰህ ፡ ሁናቴዬን ፡ ተመልከት ። ሳልሞት ፡ በሕይወቴ ፡ በጥላህ ፡ ስር ፡ መቀመጤን፡ እይ ፡ ምስክር ፡ ሁነኝ ።

አንች ፡ ፀሐይ ፡ ብርሃንሽን ፡ ዘርግተሽ ፡ ሁሉንም ፡ በትክክል ፡ የምታዪ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍጡር ፡ አንቺም ፡ በሕይወት ፡

ለመኖሬ ፡ ምስክር ፡ ሁኚኝ ፤ እናንት ፡ ዓይኖቼ ! እግዚአብሔር ፡ የፈጠረውን ፡ ፍጥረት ፡ በግዙፍ ፡ እያየችሁ ፡ በሕልምህ ፡ ትቀባዥራለህ ፡ አትበሉኝ ፡ መኖሬን ፡ አረጋግጡ ፡ እናንት ፡ በጥንቃቄ ፡ የተጌጣችሁ ፡ ጆሮዎቼ ፡ የምትሰሙትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አልሰማንም ፡ አትበሉ ፡ በሕይወት ፡ መኖሬን ፡ መስክሩ ። ጉልበቴም ፡ ተራመድ ! አይዞህ ፡ እጆቼም ፡ ተንቀሳቀሱና ፡ በሕይወት ፡ መኖራችሁን ፡ አረጋግጡ ። የደም ፡ ሥሬም ፡ አትቁም ! ሥራህን ፡ ቀጥል ፡ መላሴም ፡ ተናገር ! የተፈጠርኸው ፡ ለዚሁ ፡ ነውና ! አእምሮዬም ፡ ሥራህን ፡ አታቁም ፡ ተመራመር ። »

ማርና ፡ ቅጠሉ ፡ ፀሐዩ ፡ ለመኖሬ ፡ ምስክር ፡ እንዲሆኑኝ ፡ ከጠየቅኋቸው ፡ በኋላ ፡ ከሰውነቴ ፡ ክፍሎች ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ጠቅሼ ፡ ሥራቸውን ፡ እንዳያቆሙ ፡ መክሬ ፡ ከተቀመጥኩበት ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ብድግ ፡ ስል ፡ በመቀመጥ ፡ ብዛት ፡ አዞሮኝ ፡ ወደቅሁ ። ዓይኖቼ ፡ አላይ ፡ አሉኝ ፡ ጆሮዎቼ ፡ የንብ ፡ ድምፅ ፡ የመሰለ ፡ ጩኸት ፡ ያሰሙኝ ፡ ጀመር ። አእምሮዬም ፡ በትክክል ፡ ማስተዋል ፡ አልቻለም ። በጠቅላላው ፡ ስመክራቸው ፡ የቆየሁት ፡ የሰውነት ፡ ክፍሎቼ ፡ አልሠራ ፡ አሉ ። አሁንሳ ! ምን ፡ ልሁን ? መልሼ ፡ ወደ ፡ መጠራጠሩ ፡ ገባሁና ፡ ዛፉን ፡ እየገዘትኩ ፡ እጠይቀው ፡ ጀመር ።

« አንተ ፡ ዛፍ ፡ ተናገር !
በእግዚአብሔር ፡ ታምር ፤
የችግር ፡ ኑሮየን ፡ መከራየን ፡ መስክር ።
« የዛሬ ፡ ሥቃዩ ፡ በሕልሜ ፡ አይደለም !

በውኔ ፡ ነው ፡ እንጅ ፤
ረዳት ፡ የለኝም ፡ እንዲሁም ፡ ወዳጅ ፤

« አንተ ፡ ዛፍ ፡ ተናገር ፡ ሁሉንም ፡ ለይተህ ፤
ከታች ፡ ሥርህን ፡ ሰደህ !
በቅርንጫፍ ፡ ተከበህ !



ቅጠልኽን ፡ አስፋፍተህ !
ንቀህ ፡ አትተወኝ ፡ ማጌጥህን ፡ አይተህ ።
« አንተ ፡ ዛፍ ፡ ተናገር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታምር ፤
የችግር ፡ ኑሮየን ፡ መከራየን ፡ መስክር ።
« አንተ ፡ ዛፍ ፡ ተናገር ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ አትይ ፤
ከሥርህ ፡ ያለሁት ፡ መከራየን ፡ ለይ !
« አንተ ፡ ዛፍ ፡ ተናገር ፡ መልስ ፡ ስጠኝ ፡ ምነው !
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ዝምታ ፡ የክፋት ፡ ትርጉም ፡ ነው ።

« ታምረኛው ፡ አምላክ ፡ ዛፉን ፡ አናግርልኝ ፤
ወይም ፡ ሁናቴየን ፡ በቃልህ ፡ ለይልኝ ፡ » በማለት ፡ እየቀባጠርኩ ፡ ያንን ፡ ዱዳ ፡ ዛፍ ! ያ ፡ ወደላይ ፡ ከመቀውለል ፡ በቀር ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ የማያየውን ፡ ዛፍ ፡ ተቆርጦ ፡ ለማገዶና ፡ ለሰው ፡ ጥቅም ፡ የሚውለውን ፡ ዛፍ ! በእኔ ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ አፍ ፡ አብቅሎ ፡ ለችግሬ ፡ መፍትሔ ፡ እንዲሰጠኝ ፡ አፋጥጬ ፡ እጠይቀው ፡ ጀመር ። የዛፉን ፡ መልስ ፡ ላንድ ፡ ጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ ጠብቄ ፡ ጥያቄዎቼን ፡ ውጦ ፡ ዝም ፡ ሲል ፡ የተቀመጥኩባትን ፡ ሥፍራ ፡ « አንች ፡ - - - ምድር ፡ » እላት ፡ ጀመር ። «አንች ፡ ምድር ፡ እኔ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ሆኜ ፡ በምኖርበት ፡ ጊዜ ፡ ኤፍሬም ፡ ተብዬ ፡ በስም ፡ ያጌጥኩት ፡ ካንቺ ፡ ቆርሶ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዳምን ፡ ከፈጠረ ፡ በኋላ ፡ እኔም ፡ የአዳም ፡ ዘር ፡ ነህ ፡ የምባል ፡ አዳም ፡ ዘሩን ፡ እያበረከተ ፡ በየጊዜው ፡ ወዳንችው ፡ የሚመልስ ፡ ስለሆነ ፡ እኔም ፡ ዛሬ ፡ ወይም ፡ ነገ ፡ ከመኖር ፡ ወደ ፡ አለመኖር ፡ የምመለስ ፡ ወገንሽ ፡ አፍ ፡ አውጥተሽ ፡ ለጥያቄዎቼ ፡ መልስ ፡ ስጭኝ ። አንተም ፡ ድንጋይ ! የዝናብ ፡ ኃይልም ፡ ሆነ ፡ የፀሐይ ፡ ኃይል ፡ የማይበግሩህ ! ድንጋይነትህን ፡ የማይለውጡህ ፡ ኃይለኛ ፡ ፍጡር ! ለጥያቄዎቼ ፡ መልስ ፡ ስጥ ፤ ውቅያኖስ ፡ ባሕሩ ፤ ወንዙ ፡ ሸንተረሩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ተናገሩ ፡ ለጥያቄዎቼ ፡ መልስ ፡ ስጡ ! ከባድ ፡ ጥያቄዎች ፡ የሉኝም ፡ እኔን ፡ ከብደውኛል ፡ እንጂ ! እኮ ፡ ልጠይቅ ፡ ወይ ? ጠይቅ ፡ በሉኝና ፡ ልጀምር ! » ብዬ ፡ ስጮህ ፡ የገደል ፡ ማሚቱ ፡ ድም

ጄን ፡ በየምፍራው ፡ አስተጋባችልኝና ፡ የጠየቅኋቸው ፡ ሁሉ ፡
«አዎን ፡ አዎን ! አዎን ! » ብለው ፡ የመለሱልኝ ፡ መስሎኝ ፡
በታምር ፡ ያናገረልኝን ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ በመስጠት ፡
የድካም ፡ ፈገግታዬን ፡ ለምድራቱ ፡ ካሳየሁ ፡ በኋላ ፡ ጥያቄየን ፡
ቀጠልኩ ፤

፩ኛ/ በዓለም ፡ ላይ ፡ ያለሁት ፡ በሕልሜ ፡ ነው ? ወይስ ፡
በውኔ ?

፪ኛ/ እግዚአብሔር ፡ የፈጠረኝ ፡ የአዳም ፡ ዘር ፡ ነኝ ? ወይስ፡
እኔ ፡ ከአዳም ፡ ያልተፈጠርኩ ፤ አዳም ፡ ከበደለው ፡
በደል ፡ ይበልጥ ፡ ፈጣሪዬን ፡ ያስቀየምኩ ፡ ልዩ ፡
ፍጡር ፡ ሆኜ ፡ በኃጢአት ፡ ምክንያት ፡ ከምድር ፡ ጥቅ
ም ፡ የማልሳተፍ ፡ ሌላ ፡ እርኩስ ፡ ኃይል ፡ የፈጠረኝ ፡
ሰው ፡ ነኝ ?

፫ኛ/ በእውነትም ፡ የአቶ ፡ ወንድ ፡ ይፍራውና ፡ የወይዘሮ ፡
የዓይኔ ፡ አበባ ፡ ልጅ ፡ ሆኜ ፡ እነሱም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡
በሞት ፡ ስለተለዩ ፡ መጠጊያ ፡ ያጣሁ ፡ መናጢ ፡ ደሀ ፡
ነኝን ? አሁን ፡ እዚህ ፡ የተቀመጥኩት ፡ መድረሻ ፡
አጥቼ ፡ ርቦኝ ፡ በወሀ ፡ ጥም ፡ ተቃጥዬ ፡ እንደተቀመጥኩ ፡ ይሰ
ማኛልና ፡ ይህስ ፡ እውነት ፡ ነውን ? በይ ፡ ምድር ፡ ተናገሪ ! በይ ፡
እኮ ፡ መልስ ፡ ስጭኝ ! እሺ ፡ በል ፡ አንተ ፡ ድንጋይ ! ምናልባት፡
በእድሜ ፡ ከምድር ፡ ትበልጥ ፡ እንደሆን ፡ ተናገር ! ተናገር ፡
እንጂ ! በሉ ፡ እሺ ፡ ማነው ፡ ታላቅ ፡ ከእናንተ ? ወኃ ! ምድር !
ድንጋይ ! በሉ ፡ እኮ ! ! » እያልኩ ፡ በቁጣ ፡ ስጮህ ፡ እንደቀድ
ሞው ፡ የገደል ፡ ማሚቴ ፡ ድምጼን ፡ ተቀብላ ፡ ከምሥራቅ ፡ ወደ ፡
ምዕራብ ፡ ከሰሜን ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ታስተጋባልኝ ፡ ጀመር ። በዚ
ህም ፡ ጊዜ ፡ በቋንቋ ፡ ያልተግባባን ፡ መሆናችንን ፡ እንጂ ፡ ተጠ
ያቂዎቼ ፡ ሁሉ ፡ በማላውቀው ፡ ቋንቋ ፡ መልስ ፡ የሰጡኝ ፡ መሰ
ለኝ ። መልሶቹ ፡ ግን ፡ ሁሉም ፡ « አዎን ! አዎን ! የሚሉ ፡ ይመ
ስሉ ፡ ነበርና ፡ ጥያቄዎቼ ፡ በሙሉ ፡ በአዎን ፡ የሚመለሱ ፡ አልነ



በሩም ። በተለይም ፡ የሁለተኛውና ፡ የሦስተኛው ፡ ጥያቄዎች ፡
መልስ ፡ አዎን ፡ ከሆነ ፡ እኔን ፡ መልሶ ፡ የሚያሳብደኝና ፡ ተስፋ ፡
የሚያስቆርጠኝ ፡ ነበር ። ለመጀመሪያው ፡ ጥያቄ ፡ ግን ፡ አዎን ፡
የሚለው ፡ መልስ ፡ በመኖርና ፡ ባለመኖር ፡ መሀከል ፡ አንድ ፡
ልዩ ፡ ትርጉምን ፡ የሚፈልግ ፡ ነበርና ፡ ይህ ፡ ለእኔ ፡ ሳይስማማኝ ፡
አልቀረም ። በእርግጥ ፡ እኖራለሁ ፡ ብዬ ፡ መኖሬን ፡ ያላረጋገጥ
ኩና ፡ የለሁምም ፡ ብየ ፡ አለመኖሬን ፡ ባለማረጋገጤ ፡ በመኖ
ርና ፡ ባለመኖር ፡ መሀከል ፡ እንዳለሁና ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ አኗ
ኗር ፡ ትርጉሙን ፡ ወይም ፡ ስሙን ፡ ምን ፡ ብዬ ፡ እንደምጠራው ፡
ባለማወቂ ፡ የምጨነቅ ፡ ከመሆኔ ፡ ሌላ ፡ መልሱ ፡ የእኔን ፡ ሁናቴ፡
ይመስል ፡ ነበር ።

እራሴን ፡ በሁለቱ ፡ ጉልበቶቼ ፡ መሀል ፡ ሰድጄ ፡ እጆቼን ፡
አጣምሬና ፡ ቁልፍልፍ ፡ ብዬ ፡ እዚአቹ ፡ እተቀመጥኩበት ፡ ሥፍ
ራ ፡ እንዳለሁ ፡ ሳብሰለሰል ፡ እንቅልፍ ፡ ይዞኝ ፡ ጭልጥ ፡ አለ ።
ከምሽቱ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ከእንቅልፌ ፡ ስነቃ ፡ ከንፈ
ሮቼ ፡ ክው ፡ ብለው ፡ ደርቀው ፡ ምራቂ ፡ አልዋጥ ፡ ብሎኝ ፡ ልፍ
ስፍስ ፡ ብዬ ፡ ከባድ ፡ ሥራን ፡ ሲሠራ ፡ እንደዋለ ፡ ሰው ፡ ጠቅላ
ላው ፡ ሰውነቴ ፡ የተቀጠቀጠ ፡ መስሎ ፡ አገኘሁት ። « ለምን ፡
እንደዚህ ፡ ሆንኩ ? » ብዬ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመጠየቅ ፡ አን
ገቴን ፡ ቀና ፡ ባደርግ ፡ የፀሐዩ ፡ ብርሃን ፡ ጠፍቶ ፡ የጊዜው ፡ ሁና
ቴ ፡ ከመተኛቴ ፡ በፊት ፡ ከነበረው ፡ ብሶ ፡ በፀሐይ ፡ ፈንታ ፡ ኮከ
ቦች ፡ በሙቀት ፡ ፈንታ ፡ ብርድ ፡ በሰው ፡ ፈንታ ፡ የዱር ፡
አራዊት ፤ በጠቅላላው ፡ ልውጥውጥ ፡ ብሎ ፡ አገኘሁት ። ቀን ፡
አርቀው ፡ ያዩ ፡ የነበሩት ፡ ዓይኖቼ ፡ እዩ ፡ ብላቸው ፡ ወደ
ላይ ፡ አንጋጥጠው ፡ የኮከቦችን ፡ ጭላንጭል ፡ ሊጠቅማቸው ፡
የማይችለውን ፡ ብርሃን ፡ ከመመልከት ፡ ሌላ ፡ የምድሩን ፡ ሲሣይ
አናይም ! አሻፈረን ፡ አሉኝ ። ጆሮዎቼም ፡ አስቀድመው ፡ ይሰ
ሟቸው ፡ የነበሩት ፡ የሰው ፡ የመኪናው ፡ የጋሪውና ፡ እንደዚ
ሁም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድምጾችን ፡ ለውጠው ፡ የጅቦችን ፡ ጐሽምታ ፡
የእንቁራሪቶችን ፡ ጭርታ ፡ የመሳሰሉትን ፡ ድምፅ ፡ ካልሰማን ፡

አሉኝ ። ብድግ ፡ ብዬ ፡ ተነሣሁና ፡ ለመራመድ ፡ ብሞክር ፡ ቀን ፡ ያለችግር ፡ ይታዘዙልኝ ፡ የነበሩት ፡ እግሮቼ ፡ በጥርጣሬ ፡ ካል ሆነ ፡ ተነስተን ፡ አንወድቅም ፡ አሉኝ ። በኃይል ፡ ደነገጥኩና ፡ የገዛ ፡ ሰውነቴን ፡ ሁናቴ ፡ ለመመልከት ፡ ከኪሴ ፡ አንዲት ፡ ትንሽ ፡ መስታወትን ፡ አውጥቼ ፡ ልመልከት ፡ ብል ፡ መስታወቱ ፡ አላሳይ ፡ አለኝ ። « እንዴ ፡ ቀን ፡ ያልነበረኝን ፡ መልክ ፡ እየጨመረ ፡ ያጋንንልኝ ፡ የነበረው ፡ መስታወት ፡ አሁን ፡ ምን ፡ ነካብኝ ? ይገርማል ! በእኔና ፡ በመስታወቴ ፡ መካከል ፡ እንኳን ፡ አለመግባባት ፡ እንዲኖር ፡ ያ ፡ ተንኰለኛ ! ያ ፡ የኀብረት ፡ መጋኛ ፡ ሰይጣን ፡ ያ ፡ እርኩስ ፡ ሰይጣን ፡ እመካከላችን ፡ ጥልቅ ፡ ብሎ አለያይቶናል ፡ ማለት ፡ ነው ? አይ ፡ መከፋፈል ፡ ይገርማል ! በልተው ፡ አንተ ፡ መስታወት ! ግፋ ፡ ቢል ፡ ልታገለግለኝ ፡ ትችል የነበረው ፡ የገዛ ፡ መልኬን ፡ ጉስቁልና ፡ ያጠቃው ፡ ሰውነቴን ፡ አመድ ፡ የለበሰው ፡ ፊቴን ፡ ዓለምን ፡ አካላይ ፡ የመሰሉት ፡ ችግር ፡ ያጋለጣቸው ፡ ሥርቼን ፡ በችግር ፡ የበለዙት ፡ ዓይኖቼን ፡ ያለ ፡ ሥጋ ፡ ሐውልት ፡ መስሎ ፡ የቆመው ፡ አፍንጫዬን ፡ ደሙ ፡ የተሚጠጠው ፡ ሰውነቴን ፡ ከማሳየት ፡ በስተቀር ፡ ምን ፡ ልታመለክተኝ ፡ ኖሮአል ? በል ፡ ባትግባባ ፡ ተወው ! » ብዬ ፡ መስታወቱን ፡ ወረወርኩት ። አሁንም ፡ አንገቴን ፡ ቀና ፡ አድርጌ ፡ ወደ ፡ ሰማዩ ፡ ብመለከት ፡ ሰማዩ ፡ ፈንጣጣ ፡ እንደጠቀጠቀው ፡ ፊት ፡ መስሎ ፡ አቅም ፡ ባነሰው ፡ ብርሃን ፡ አጊጦ ፡ ከማገገም ፡ ወደ ፡ ብሶት ፡ እንደሚሄድ ፡ ኃይል ፡ ሆኖ ፡ አየሁት ። የሰማዩ ፡ ሁናቴ ፡ እንደ ፡ እኔው ፡ የደከማ ፡ አረማመድ ፡ መስሎ ፡ ስለታየኝ ፡ ተኝቼ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ያለምኳቸው ፡ ሕልሞች ፡ እንዳሉ ፡ ለማስተዋል ፡ አሳቤን ፡ መለስ ፡ አደረግሁ ።

ምናልባት ፡ በድካም ፡ ምክንያት ፡ ኃይለኛ ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዶኝ ፡ ነበር ፡ መሰለኝ ፡ ለጊዜው ፡ ትዝ ፡ የሚለኝን ፡ ሕልም ፡ አጣሁና ፡ እሱኑ ፡ ሳሰላስል ፡ በውኔ ፡ አንድ ፡ የምኞት ፡ ሕልም ፡ ኰተፍ ፡ አለልኝ ።



## የምኞት ፡ ሕልሜ ።

የምኞት ፡ ሕልሜም ፡ ልክ ፡ ሃያ ፡ ዓመት ፡ እንደሞላኝ ፡ ወይዘሪት ፡ ዓለሜ ፡ የምትባል ፡ አንዲት ፡ ቆንጆ ፡ ልጅ ፡ እመንገድ ፡ አገኝና ፡ ኰራ ፡ ባለ ፡ አነጋገር ፡ « አንቺ ! እንደምን ፡ ዋልሽ ? » አልኳትና ፡ ድምፅ ፡ ሳትሰጠኝ ፡ ዞር ፡ ብላ ፡ ተመለከተችኝ ። ፈገግታዋ ፡ ግሩም ፡ ስለነበረ ፡ ፈገግታው ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ጥሩ ፡ አቀባበልና ፡ እሺታ ፡ ቆጠርኩትና ፡ ንግግሬን ፡ ቀጠልኩ ። ሳቅ ፡ አለችልኝ ! እቺስ ፡ የትዳር ፡ ጓደኛዬ ፡ በሆነች ፡ አልኩ ። የዕለቱ ፡ የውኔ ፡ ቅዠት ፡ ድኅነቴን ፡ አላስረሳኝም ፡ ነበርና ፡ « ብንጋባስ ፡ ምን ፡ በልተን ፡ ምን ፡ ለብሰን ፡ በምን ፡ ተደግፎ ፡ እምንስ ፡ ውስጥ ፡ እንኖራለን ? » ብዬ ፡ ሳስብ ፡ በውኑ ፡ የሚቃዥ ፡ ሰው ፡ ከእውነተኛ ፡ የእንቅልፍ ፡ ሕልም ፡ ይብስ ፡ አንዱን ፡ ትቶ ፡ ወዳንዱ ፡ መራመድ ፡ አያዳግተውምና ፡ ከዚች ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ እንዴት ፡ እንደተቀራረብንና ፡ እንዴት ፡ እንደተጋባን ፡ ሳላረጋግጥ ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለድን ። ያ ፡ ላገሩ ፡ ደሙን ፡ ያፈሰሰውን ፡ የትም ፡ ወድቆ ፡ የቀረውን ፡ አባቴን ፡ ለማስታወስ ፡ የልጁን ፡ ስም ፡ «ወንድ ፡ ይፍራው» ፡ እንበለው ፡ ብዬ ፡ ሚስቴን ፡ ለመንኳትና ፡ እስዋም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያክብራት ፡ «እሺ ፡ ምን ፡ ከፋኝ» ብላኝ ፡ ሕጻኑ ፡ «ወንድ ፡ ይፍራው ፡ ኤፍሬም» ተባለ ። በዚሁ ፡ በመደሰት ፡ ላይ ፡ እያለን ፡ መንፈቅ ፡ ይሁን ፡ ዓመት ፡ ሳንቆይ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ደገምንና ፡ የዓይኔ ፡ አበባ ፡ እንድንላት ፡ ሚስቴን ፡ እንደገና ፡ ብለምናት ፡ አሁንም ፡ ያለቅሬታ ፡ ተቀበለችኝና ፡ ልጅቷ ፡ «የዓይኔ ፡ አበባ ፡ ኤፍሬም» ፡ ተባለች ።

የእኔ ፡ ወላጆች ፡ የልጆቼ ፡ አያቶች ፡ ስማቸው ፡ እንዳይረሳ ፡ በውኔ ፡ አለምኩላቸውና ፡ በልጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ ስማቸው ፡ ይጠራ ፡ ጀመር ። ሳይቸግረው ፡ ባያቱ ፡ ሊጠራ ፡ የማይችል ፡ ሦስተኛ ፡ ልጅ ፡ ተወለደና ፡ ማን ፡ ይባል ? እኔም ፡ እናቱም ፡ ለልጃችን ፡ ስም ፡ ለመስጠት ፡ « አስብ ፡ አስቢ » እንባባል ፡ ጀመር ። ኑሮአችንን ፡ የሚመስል ፡ ስም ፡ እንጂ ፡ የፈለግነውን ፡ ብንለው ፡ የስም ፡ ነፃነት ፡ እንዳለን ፡ እናውቃለን ። ዓለሜ ፡ « ልጃችንን ፡

ተለባብሶ ፡ ኑሮ ፡ » እንበለው ፡ አለችኝ ። እኔም ፡ « እንዴት ! ተለባብሶ ፡ ኑሮ ፡ ትይዋለሽ ? » ስሙ ፡ ተስማሚ ፡ አይደለም ! » ብላት ፡ ? « የሁለቱን ፡ ልጆቼ ፡ ስም ፡ አንተ ፡ ሰየምክ ፤ ለምን ፡ እኔንስ ፡ እሺ ፡ አትለኝም ? ኑሮአችን ፡ ያልተቃወመውን ፡ ስም ፡ አንተ ፡ ለምን ፡ ትቃወማለህ ? » ብላ ፡ ወደ ፡ ማምረሩ ፡ ስታመራ « ኧረ ፡ ተይ ፡ ላጠራሩ ፡ አይመችም ! እንዴት ፡ ተለባብሶ ፡ ኑሮ ፡ ኤፍሬም ፡ ትይዋለሽ ? ባንቺ ፡ ስም ፡ አይጠራ ! እኔ ፡ ግሩም ፡ ስም ፡ ኖሮኝ ፡ እንዴት ፡ በተለባብሶ ፡ ታጌጪኝ ? » ብላት ፡ አይሆንም ፡ ብላ ፡ ችክ ፡ አለችብኝና ፡ « በይ ፡ እሺ ፡ ይሁንልሽ ! ተለባብሶ ፡ ኑሮ ፡ በይው ፡ » ተባብለን ፡ በዚሁ ፡ ስም ፡ ይጠራ ፡ ጀመር ።

ገና ፡ በተለባብሶ ፡ ኑሮ ፡ እንደተስማማን ፡ ልጁ ፡ በኃይል ፡ ይጮሃል ፤ እኔም ፡ « ኧረ ፡ ተይ ፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ ተለባብሶ ፡ ኑሮ ፡ አልተስማማውም ፤ ለዚህ ፡ ነው ፡ አቤት ፡ የሚለው ! ምን ፡ አለ ፡ የልጁ ፡ ስም ፡ ቢለወጥ ፡ ጠቅላላው ፡ የኑሮአችን ፡ ሁናቴ ፡ አይለወጥ ፤ ለምን ፡ ችክ ፡ ትያለሽ ? » ብዬ ፡ ተናድጄ ፡ ስጮህባት ፡ ባነንኩ ! ባነንኩ ? ከምን ? ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ ሲሳይ ! እንቅልፍማ ፡ አልተኛሁ ! ሰው ፡ በውኑ ፡ አልሞ ፡ ይባንናል ? «አሁን ፡ ገና ፡ ጉድ ፡ ሆንኩ ! » እያልኩ ፡ አካባቢዬን ፡ እመለከት ፡ ጀመር ።

የአሳብ ፡ ባለትዳር ፤ የአሳብ ፡ ባለልጅ ፡ ከእንቅልፍ ፡ ሳይሆን ፡ በውኔ ፡ ስባንን ፡ ጊዜው ፡ ከምሽቱ ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ስቃይ ፡ ስተራመስ ፡ ከቆየሁ ፡ በኋላ ፡ ለሕይወቴ፡አንድ ፡ ብሃልት ፡ እንድፈጥርለት ፡ ተገደድኩ ። ይኸውም ፡ የሕልሜን ፡ ደስታ ፡ ዘጠና ፡ በመቶ ፡ እንደሆነ ፡ ወሰድኩት ። የውኔ ፡ ችግር ፡ ደግሞ ፡ ዜሮ ፡ በመቶ ፡ እንዳይሆን ፡ ሕይወት ፡ አለኝና ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ በመቶ ፡ ያህል ፡ አደረግሁት ። እንግዲህ ፡ የሕልሜ ፡ ደስታና ፡ የውኔ ፡ ኑሮ ፡ ተደምረው ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሁለት ፡ ሆኑልኝና ፡ የኔ ፡ ጠቅላላ ፡ የኑሮ ፡ ሁናቴ ፡ አማካይ ፡ ቁጥር ፡ አምሳ ፡ አንድ ፡ በመቶ ፡ ደረሰልኝ ! «እንዴ ! ከዚህ ፡ በላይ ፡ ምን ፡ ፈለግሁ ? ሰማይን ፡ በእጄ ፡ መጨበጥ ፡ ነውን ? ብዙ ፡ አልተማርኩ !



አጋር ፡ የለኝ ! ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ የለኝ ! ለእኔ ፡ ኑሮ ፡ አምሳ ፡ አንድ ፡ በመቶ ፡ መቼ ፡ አነሰው ? » እያልኩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ላለማማረር ፡ ወስኜ ፡ «ተመስገን ! የአገሬን ፡ ነጻነት ፡ ጠብቅልኝ ፡» እለው ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ራሴን ፡ በራሴ ፡ ማታለልና ፡ ውጣ ፡ ውረድ ፡ ከሥሩ ፡ የተቀመጥኩበትን ፡ ዛፍ ፡ ልብስና ፡ ከለላ ፡ አድርጌ ፡ ለሊቱን ፡ አነጋሁና ፡ ጠዋት ፡ ገና ፡ ጎሕ ፡ ሳይቀድ ፡ ወደ ፡ ንፍሮዬ ፡ ገሰገስኩ ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ችግርና ፡ አንዳንዴም ፡ በልመና ፡ ዓመት ፡ አለፈኝ ። እንግዲህ ፡ አንድ ፡ የኑሮ ፡ ለውጥ ፡ እስካገኝሁ ፡ ድረስ ፡ የኔ ፡ ኑሮ ፡ ባንድ ፡ ጭልፋ ፡ ንፍሮና ፡ በልመና ፡ የተወሰነ ፡ መሆኑን ፡ ተገነዘብኩ ። በለውጡ ፡ በኩል ፡ ስመለከተው ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ ያለወጥኩት ፡ ዕድል ፡ በራሱ ፡ ወይም ፡ በታምር ፡ ይለወጣል ፡ ማለት ፡ ዘበት ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፡ ከከተማ ፡ ኑሮ ፡ ወደ ፡ ባላገር ፡ ብሄድና ፡ የመንደርን ፡ ልጅ፡ ሰብስቤ ፡ ባስተምር ፡ በመጠኑ ፡ በልቼ ፡ ለማደር ፡ የምችል ፡ መሰለኝና ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ አገሬ ፡ ለመሄድ ፡ ወሰንኩ ። የአባ ፡ ንፍሮም ፡ እንዳልሞት ፡ እንዳልሸር ፡ አደረገኝ ፡ እንጂ ፡ ሌላውን ፡ ልተውው ፤ ሆኖም ፡ ውለታው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

በየበረንዳውና ፡ በየዛፉ ፡ ሥር ፡ ውዬ ፡ በማደር ፡ ባንዲት ፡ ጭልፋ ፡ ንፍሮ ፡ ሕይወቴ ፡ ተይዛ ፡ ነጻ ፡ ወኃዬን ፡ እየጠጣሁና ፡ አንዳንዴም ፡ ጨርሶ ፡ ሲብስብኝ ፡ ጥጉን ፡ ይዤ ፡ ባጠናኋቸው ፡ የበዓላት ፡ ስም ፡ እየተጠቀምኩ ፡ በመለመን ፡ ብዙ ፡ ቀኖችን ፡ ካሳለፍኩ ፡ በኋላ ፡ ምድሪቱንና ፡ ዛፎችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታምር ፡ እንዲናገሩልኝ ፡ በጠየቅሁ ፡ ልክ ፡ በዓመቴ ፡ ዜና ፡ ማርቆስ ፡ ገዳም ፡ ደረስኩ ።

# ኤፍሬም ፡ በዜና ፡ ማርቆስ ።

ዜና ፡ ማርቆስ ፡ ከተወለድኩበት ፡ ቀበሌ ፡ ከገደባኖ ፡ የሦስት ፡ ሰዓት ፡ መንገድ ፡ ርቆ ፡ የሚገኝ ፤ እናቴ ፡ እኔ ፡ የላኩላትን ፡ ደብዳቤ ፡ ለማስነበብ ፡ ሔዳ ፡ ወለቴን ፡ በመርዳት ፡ የጉልበት ፡ አገልግሎት ፡ የሰጠችበት ፣ የባላገር ፡ ገዳም ፡ ነው ። ባካባቢው ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ አባቴን ፡ ያውቁ ፡ ነበርና ፡ ገና ፡ እንደደረስኩ ፡ « የወንድ ፡ ይፍራው ፡ ልጅ ፣ የሙት ፡ ልጅ ፡ ምነው ፡ እንደዚህ ፡ ሰውነትህ ፡ አልቋል ?» እያሉ ፡ ለጊዜው ፡ ሁሉም ፡ ባለው ፡ መጠን ፡ ይጋብዘኝ ፡ ጀመርና ፡ ይህን ፡ ሳይ ፡ ፍንክች ፡ ከተማ ፡ ውስጥ የቆየሁበትን ፡ ዘመን ፡ እረግም ፡ ጀመር ።

ወደ ፡ አንዳንዶች ፡ የአገር ፡ ሽማግሌዎች ፡ ቤት ፡ ሔጄ ፡ ልጆቻቸውን ፡ ማስተማር ፡ የሚፈልጉ ፡ ቢኖሩና ፡ መጠነኛ ፡ ገንዘብም ፡ ከሕዝቡ ፡ እየተዋጣ ፡ ቢከፈለኝ ፡ መልካም ፡ አገልግሎትን ፡ ለመስጠት ፡ የምችል ፡ መሆኔን ፡ ገለጽኩላቸው ። የመንደሩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ «ልጆቻችን ፡ የእኛን ፡ ዕድል ፡ እንዲገጥማቸው ፡ ከመጠበቅ ፡ ተምረው ፡ ዳዊት ፡ ቢደግሙ ፡ ኑሮአቸው ፡ ይሻሻላል ፣ » እያሉ ፡ ሰውን ፡ አግባብተውት ፡ ለጊዜው ፡ ሃያ ፡ ሰባት ፡ ቤተሰብ ፡ ልጁን ፡ ለማስተማር ፡ ተስማማ ። የክፍያው ፡ መጠን ፡ አንድ ፡ ቁና ፡ ገብስ ፣ ወይም ፡ ግማሽ ፡ ቁና ፡ ስንዴ ፣ ገብስና ፡ ስንዴም ፡ መስጠት ፡ የማይመቸው ፡ ወላጅ ፡ ግማሽ ፡ ቁና ፡ አተር ፡ ወይም ፡ ሃያ ፡ ሳንቲም ፡ እንዲከፍሉ ፡ ተደረገ ። ስምምነቱ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ወይም ፡ ወይሞች ፡ ስለነበሩ ፡ የገብሱ ፣ የስንዴው ፣ የአተሩ ፣ እናም ፡ የሣንቲሙ ፡ ልክ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሚሆንልኝ ፡ ላውቅ ፡ ባልችልም ፡ ጠቅላላ ፡ አሳቡ ፡ በጣም ፡ አስፈነደቀኝ ፤ ቢሆንም ፡ የውስጤ ፡ ደስታ ፡ ውጭ ፡ እንዲታይብኝ ፡ አልፈለግሁምና ፡ ሲነገረኝም ፡ ቅር ፡ እንደተሰኘ ፡ ሰው ፡ በመምሰል ፡ « መቼም ፡ ችግር ፡ ስላለብኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በነጻስ ፡ ቢሆን ፡ ማስተማር ፡ ይገባኝ ፡ አልነበረምን ? ግድ ፡ የለም ፡



ይሁን ፡ » ብዬ ፡ በቅሬታ ፡ መልክ ፡ መዋጮየን ፡ ለመቀበል ፡ ተስማማሁ ።

ከሃያ ፡ ሰባት ፡ ቤተሰቦች ፡ አርባ ፡ አራት ፡ ልጆች ፡ ለትምህርት ፡ መዘጋጀታቸውን ፡ ተረዳሁ ። የአገሩ ፡ ባላባት ፡ በየዓመቱ ፡ ዜና ፡ ማርቆስ ፡ በሚከበርበት ፡ ዕለት ፡ ድግስ ፡ የሚያበሉበትን ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ አዳራሽ ፡ ለማስተማሪያ ፡ ክፍል ፡ እንዲሆን ፡ ፈቀዱልኝ ። በልጆቹ ፡ ቁጥር ፡ ልክ ፡ ፊደሎች ፡ ከሩቅ ፡ አስገዝቼ ፡ አስመጣሁ ፤ ለእኔ ፡ ለመምህሩ ፡ አንዲት ፡ ባርጩማ ፡ ከባላባቱ ፡ ተላከልኝና ፡ ተማሪዎቼን ፡ አፈሩ ፡ ላይ ፡ አስቀምጬ ፡ ሀ ፡ ሁን ፡ ማስቆጠር ፡ ጀመርኩ ። እኔን ፡ « የኔታ ፡ ብለው » ሲጠሩኝ ፡ እኔ ፡ መምህሮቼን ፡ እጠራ ፡ በነበረው ፡ ዓይነት ፡ «ቲቸር» ፡ ብለው ፡ እንዲጠሩኝ ፡ አዘዝኳቸውና ፡ ቲቸር ፡ ለመባል ፡ ወግ ፡ ደረሰኝ ። የኔታም ፡ አነስተኛ ፡ ስም ፡ አልነበረም ፤ ሰዓት ፡ ስላልነበረኝ ፡ ጊዜውን ፡ በጥላዬ ፡ እየለካሁ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ እንወጣና ፡ የሰውነትን ፡ ማጠንከሪያ ፡ ትምህርት ፡ አስተምራቸው ፡ ስለነበረ ፡ ልጆችና ፡ ወላጆች ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሆኖባቸው ፡ በጣም ፡ ያደንቁኝ ፡ ጀመር ። ሆ ፡ ብዬ ፡ ሳላርስ ፡ ገብሱ ፣ ስንዴው ፣ አተሩ ፣ ጥሬ ፡ ገንዘቡ ! ከየስፍራው ፡ እየጐረፈልኝ ፡ ባንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ መራመድ ፡ አቅቷቸው ፡ የነበሩት ፡ እግሮቼ ፡ ጠንክረው ፡ መላው ፡ ሰውነቴ ፡ ተሻሽሎ ፡ ሌላ ፡ መስያለሁ ፡ « ለካስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳይደግስ ፡ አልተጣላኝም ! ይህች ፡ ትንሽዋ ፡ እውቀቴ ፡ እኮ ፡ በልቼ ፡ እንዳድር ፡ አምላክ ፡ የፈጠረልኝ ፡ ጥበብ ፡ ነው ። » እያልኩ ፡ በችግሬ ፡ ጊዜ ፣ በጭንቅ ፡ በመከራዬ ፡ ወቅት ፣ ያማረርኩትን ፡ ፈጣሪዬን ፡ ማመስገን ፡ ጀመርኩ ። ወደ ፡ ሶስት ፡ ወር ፡ ከቆየሁ ፡ በኋላም ፡ እምዬ ፡ እኔን ፡ አቅፋኝ ፡ ቁጭ ፡ እንዳለች ፡ ፊቴን ፡ አይታ ፡ « ችግር ፡ አጐሳቆለህ ፡ እንጂ ፡ ቀን ፡ ቢወጣልህስ ፡ መልክህ ፡ እንዴት ፡ ውብ ፡ በሆነ ፡ ነበር ፡ » ወዳለችው ፡ ደረጃ ፡ ደረስኩ ። ተማሪዎቼም ፡ ፊደልን ፡ ጨርሰው ፡ አቡ ፡ ጊዳንና ፡ መልክተን ፡ አጋምሰዋል ።

ባራተኛው ፡ ወር ፡ ጫማና ፡ ልብስ ፡ እንደዚሁም ፡ የእጅ ፡ ሰዓት ፡ ከፍንክች ፡ ከተማ ፡ እንዲመጣልኝ ፡ ገንዘብ ፡ ልኬ ፡ በቶሎ ፡ ደረሱልኝና ፡ አጊጬ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ መታየትን ፡ ጀመርኩ ። ሚዶ ፡ አያውቅ ፡ የነበረውን ፡ ፀጉሬ ፡ በቅባት ፡ ደባብሼ ፡ እያበጠርኩና ፡ ነጣ ፡ ያሉት ፡ ልብሶችን ፡ እየቀያየርኩ ፡ በየእሁዱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ በምገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ተማሪዎችና ፡ ወላጆቻቸው ፡ የካህናትን ፡ ያህል ፡ ክብር ፡ እየሰጡኝ ፡ « ይህ ፡ እኮ ፡ የልጆቻችን ፡ አባት ፡ በጣም ፡ መወደድና ፡ መከበር ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ ነው ፡ » እያሉ ፡ ያወዳድሱኝ ፡ ጀመር ። እኔም ፡ የእነሱን ፡ ውዳሴ ፡ እየሰማሁ ፡ ልጆቻቸውን ፡ በይበልጥ ፡ እየተከታተልኩ ፡ በማስተማር ፡ አንዳንዶቹም ፡ መልክተን ፡ አልፈው፡ በጥቂቱ ፡ መጽሐፍን ፡ ማንበብ ፡ ጀመሩ ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ትምህርታቸውን ፡ የሞራል ፡ ትምህርታቸውን ፡ ለቤተ ፡ ሰቦቻቸው ፡ የሚያሳዩትን ፡ ትሕትናና ፡ መታዘዝ ፡ በሚገባ ፡ ተምረው ፡ ስለነበረ ፡ የእኔን ፡ ስም ፡ በይበልጥ ፡ ሊያስነሳው ፡ ቻለና ፡ ሰዉ ፡ ከየ ፡ ቄሱ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ልጁን ፡ እያወጣ ፡ ያመጣልኝ ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መዋጮየም ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ ሔዶ ፡ በባላገር ፡ ኑሮ ፡ ችግርን ፡ ወደ ፡ ማሰናበቱ ፡ ገደማ ፡ ደርሼ፡ ስለነበረ ፡ ያች ፡ እምየ ፡ ያቺ ፡ እድለቢስዋ ፡ እናቴ ፡ ያቺ ፡ « አባትህም ፡ እኔም ፡ ግራ ፡ ገብቶናልና ፡ ቀን ፡ ታወጣልን ፡ ይሆናል» እያለች ፡ ትመኝ ፡ የነበረችው ፡ ከርታታ ፡ ያቺ ፡ ምኞቷ ፡ ሳይሟላ አንድ ፡ ቀን ፡ እንኳን ፡ ጠግባ ፡ ሳትበላ ፡ የመኖርን ፡ ትርጉም ፡ ሳትረዳ ፡ ስለነጋ ፡ ብቻ ፡ ተመስገን ፡ እያለች ፡ ትኖር ፡ የነበረችው እምዬ ፡ ትገ ፡ ትለኝና ፡ አንጀቴ ፡ እርር ፡ ይላል ። ያ ፡ አባቴም ፡ የሀገሩን ፡ ነጻነት ፡ ለማስከበር ፡ ትጥቅና ፡ ስንቁን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ሊነሳ ፡ ሲል ፡ ፊትፊቴን ፡ እያየኝ ፡ በመባባት ፡ « አሳቤ ፡ አትባክን ፡ ምክንያት ፡ አታብዛ ፡ ነጻ ፡ መሆን ፡ የለም ፡ ያለደም ፡ በዋዛ ፡» ብሎ ፡ በመሸለል ፡ « ልጄ ፡ በሕይወት ፡ ላገኝህ ፡ » ብሎኝ ፡ የወጣውን ፡ ትገ ፡ ይለኛል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ « ነጻ ፡ መሆን ፡ የለም ፡ ያለ ፡ ደም ፡ በዋዛ ፡ » እንዳለው ፡ ጠንክሮ ፡ ተዋግቶ ፡ ከሱ ፡ የሚ



ፈለገውን ፡ ድርሻ ፡ አበርክቶ ፡ ለሀገሩ ፡ መሥዋዕት ፡ በመሆኑ ፡ ስሜቴን ፡ ከፍ ፡ ያደርገዋል ። አንዴ ፡ ሆዴ ፡ ጠግቦ ፡ ባደርኩ ፡ አንዴ ፡ እንኳን ፡ ቀን ፡ በወጣልኝ ፡ እያለች ፡ በምኞት ፡ ከሞተችው ፡ እምዬ ፡ «የሀገሬ ፡ ነጻነት ፡ እንዳይደፈርስ ፡ ደሜን ፡ አፍስሼ ጠላትን ፡ ድል ፡ አድርጌ ፡» እያለ ፡ ሲመኝ ፡ በመሞቱ ፡ የአባቴ ፡ ደም ፡ ለሀገሬ ፡ ነጻነት ፡ እግዚአብሔር ፡ የተቀበለው ፡ መሥዋዕት ፡ እንደሆነ ፡ ስለምቆጥረው ፡ ልቤ ፡ ይደነድናል ። ስለዚህ ፡ የአባቴን ፡ ሞት ፡ እንደመኖር ፡ የእምዬን ፡ ሞት ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ ሞት ፡ እቆጥረው ፡ ጀመር ።

ስድስት ፡ ወር ፡ እንደቆየሁ ፡ በጣም ፡ ተሻሽዬ ፡ ሕዝቡም ፡ በጣም ፡ ወዶኝ ፡ ሣለሁ ፡ የዜና፡ማርቆስ ፡ ገዳም ፡ ደብተራዎችና ፡ ተማሪዎች ፡ በቅናት ፡ ተነሣሱብኝ ፤ የምሠራውም ፡ የማስተማር ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ ከነሱ ፡ በልጦ ፡ ሲያዩ ፡ እኔን ፡ ማጥፊያ ፡ ዘዴ ፡ መፈለግ ፡ ጀመሩ ። የደስታዬ ፡ ዕድሜ ፡ ሳይረዝም ፡ በቅናት ፡ የተደፈነው ፡ ልባቸው ፡ የታወረው ፡ ዓይናቸው ፡ መንደሪቱ ፡ ውስጥ ፡ እሠራው ፡ የነበረውን ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ እንዲደናቀፍ ፡ አደረገብኝ ።

አንድ ፡ ቅያሬ ፡ ልብስ ፡ ሳልጨምር ፤ ላንድ ፡ ወር ፡ የሚያገለግለኝ ፡ ተቀማጭ ፡ ሳይኖረኝ ፡ እነዚህ ፡ ምቀኞች ፡ ጉድ ፡ ሊያደርጉኝ ፡ ነው ! እኛ ፡ ያላገኘነውን ፡ ለምን ፡ ያገኛል ? ለምንስ ፡ አጊጦ ፡ ይታያል ፡ እያሉ ፡ በቅናት ፡ መንፈስ ፡ ተቀሰቀሱብኝ ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ጠዋት ፡ አባ ፡ ክንዴ ፡ የሚባሉ ፡ አንድ ፡ መነኩሴ ፡ ወደ ፡ ማስተምርበት ፡ አዳራሽ ፡ ከተፍ ፡ አሉና እኔና ፡ ተማሪዎቼ ፡ ተነስተን ፡ በአክብሮት ፡ ተቀበልናቸው ። እኔን ፡ መጥተው ፡ መስቀል ፡ ያስሙኛል ፡ ብል ፡ ገልመጥ ፡ አድርገውኝ ፡ የሚያሽሟጥጡም ፡ በመምሰል ፡ ወደ ፡ ተማሪዎቼ ፡ ዞረው ፡ « ቁጭ ፡ በሉ » አሏቸውና ፡ ተቀመጡ ፤ የአንዱን ፡ ተማ

ሪ ፡ ስም ፡ ጠሩና ፡ « አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ድገም ፡ እስኪ ፡ » ፡
አሉት ፤ ቢሞክር ፡ አልቻለም ። « ሰላመ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡
መላክ ፡ በል » ፡ ቢሉት ፤ « ገብርኤልንም ፡ አልችልም ፡ »
ሲል ፡ መለሰላቸው ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ « እናንት ፡ የማርያም ፡
ጠላቶች ፤ እናንት ፡ አረመኔዎች ! ሁለተኛ ፡ ወደዚህ ፡ አዳራሽ ፡
ትመጡና ፡ ወዮ ! ገዝቼአችኋለሁ ። አንት ፡ መምህር ! ልጆ
ቻችንን ፡ ልታበላሽ ፡ ቀለብ ፡ ይሰፈርልሃል ። ቀድሞውኑ ፡ የኔታ ፡
የሚለውን ፡ ስም ፡ በመንቀፍ ፡ «ትቸር» ፡ በሉኝ ፡ ስትል ፡ የሃይማ
ኖታችን ፡ ተጻይ ፥ የባሕላችን ፡ እንቅፋት ፥ እንደምትሆን ፡ ሳን
ረዳ ፡ አልቀረንም ፡ ነበር ። በነጭ ፡ ልብስ ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡
አሸብርቀህ ፡ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረባቸውን ፡ ልጆች ፡ ለማ
ሳሳት ፡ ዳቢሎስ ፡ እዚህ ፡ አምጥቶ ፡ ጣለብን ፡ » በማለት ፡ ዞር ፡
ብለው ፡ እኔ ፡ ላይ ፡ አፈጠጡ ። እንደዚህ ፡ ለመልካም ፡ ሥራ ፡
ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፥ እንደዚህ ፡ በመልኩ ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡
የሰይጣንን ፡ ሥራ ፡ ለሚፈጽም ፡ ምቀኛ ፥ እንደዚህ ፡ ላለ ፡ በጥ
ባጭና ፡ ተንኰለኛ ፡ ማንቁርቱን ፡ ይዞ ፡ ማነቅ ፥ እዚያው ፡ እቆ
መበት ፡ አፍርጦ ፡ መርገጥ ፥ ፊቱን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ በጥፊ ፡ ማጣ
መም ፥ እንደዚህ ፡ ለራሱ ፡ ምቾት ፡ ሲል ፡ እውነትን ፡ በሃሰት ፡
ለሚለውጥ ፡ እርኩስ ፥ እንደዚህ ፡ ሃይማኖትን ፡ ደጋፊ ፡ መስሎ ፡
የሰይጣንን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ መጥፎ ፥ ለምቾቱ ፡ ብሎ ፡ የሰ
ውን ፡ ሕይወት ፡ ጨርሶ ፡ ለማጥፋት ፡ ለሚነሳ ፡ ከይሲ ፥ ያንን ፡
እርኩስ ፡ መላሱን ፡ መቁረጥ ፡ ያስፈልግ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡
« እኔ ፡ ማን ፡ ነኝ ? ምን ፡ ዓይነት ፡ ስቃይስ ፡ ሕይወቴን ፡ ሲያስጨ
ንቀው ፡ የኖርኩ ፡ ሰው ፡ ነኝ ? ቂስ ፡ አሰርኩህ ! ገዘትኩህ !
ሲለው ፡ እጅ ፡ እግሩ ፡ የሚታሰረው ፡ ሕዝብ ፡ መንኩሴውን ፡
ብቃወም ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ፍርድ ፡ ይሰጠኛል ? በኋላስ ፡ እምን ፡
ውስጥ ፡ እገባለሁ ? » እያልኩ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ውጣ ፡ ውረድ ፡
በሁለት ፡ ደቂቃ ፡ ሙግት ፡ ካመዛዘንኩ ፡ በኋላ ፡ « አባቴ ፡ ይቅ



ርታ ፡ ያድርጉልኝና ፡ አሁን ፡ ይሂዱ ! ወደፊት ፡ በሚሰጡኝ ፡
ምክር ፡ መሠረት ፡ እፈጽማለሁ ፥ ላለፈው ፡ ይቅር ፡ ይበሉኝ ፥
ይፍቱኝ ፥ ተማሪዎቼን ፡ አይገዝቷቸው ፡ ይፍቷቸው ፥ » እያልኩ ፡
ልመና ፡ ገባሁና ፡ ማናችንንም ፡ ሳይፈቱ ፡ እንዳሠሩን ፡ ውልቅ ፡
አሉ ። ተማሪው ፥ ተማር ፡ ብለው ፡ ተገዝተናልና ፡ አንማርም ፡
የሚለኝ ፡ በረከተና ፡ ግራ ፡ ገባኝ ። በብዙ ፡ ዓይነት ፡ ውዝግብ ፡
ቀኑ ፡ አለቀና ፡ ወደየቤታችን ፡ ተመለስን ። አባ ፡ ክንዴም ፡ አስ
ቸኳይ ፡ የመንግሥትን ፡ አዋጅ ፡ ይዞ ፡ እንደሚጣደፍ ፡ ሰው ፡ በየ
መንደሩ ፡ እየሮጡ ፡ « ያ ፡ ትቸር ፡ የምትሉት ፡ ሰው ፤ ልጆቻች
ሁን ፡ አባለገ ፡ እኮ ! ሃይማኖታችንን ፡ አረከሰብን ፡ እኮ ! ባሕላ
ችንን ፡ ለወጠው ፡ እኮ ! ምን ፡ ትጠብቃላችሁ ? የተቀደሰውን ፡
ስንዴ ፡ ለዚህ ፡ ለእርኩስ ፡ ሥራ ፡ እየሰፈራችሁ ፥ ገብስ ፥ አተር ፥
ገንዘብ ፡ እየሰበሰባችሁ ፡ ስታስታቅፉት ፡ እሱ ፡ በዚህ ፡ ገን
ዘብ ፡ ደኃን ፡ አይረዳበት ፥ ለምጽዋት ፡ አያወጣው ፥ እንዲያው ፡
እንደ ፡ አራዳ ፡ ቀጣፊ ፡ እየተሽሞነሞነ ፡ ልጆቻችንን ፡ ሲያ
በላሽ ፡ ነገ ፡ እኮ ፡ እናንተን ፡ አናውቅም ፡ በሚል ፡ ይነሱና ፡
እግዚአብሔርንም ፡ እስከ ፡ መካድ ፡ ይደርሳሉ ! ጾመ ፡ ድጓን ፥
ጾመ ፡ ሐዋርያትን ፥ ሰንበትን ፥ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዜማን ፥
ቅኔን ፡ የመሳሰሉትን ፡ እንደማስተማር ፡ እሱ ፡ ትቸር ፡ እየተሰኘ ፡
በየቀኑ ፡ ወታደር ፡ ይመስል ፡ ሰልፍ ፡ አውጥቶ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡
ተወዛወዙ ! ቁጭ ፡ በሉ ! ተነሱ ! ተኙ ! እግሮቻችሁን ፡ አንፈራ
ጥጡ ! ሰብስቡ ! ደረታችሁን ፡ ንፉ ! ባፍንጫችሁ ፡ ብቻ ፡ ተን
ፍሱ ! እያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፈጠራቸው ፡ ዓይነት ፡ ትክ
ክለኛ ፡ ይዞታ ፡ እንዳይኖራቸው ፡ አዳዲስ ፡ መስመር ፡ ይፈጥር
ላቸዋል ። አሁን ፡ እኔ ፡ ብዙ ፡ ልለፈልፍ ፡ አልችልም ፥ የጸሎት ፡
ጊዜየን ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ መጥሪያ ፡ ጊዜየን ፥ ላባክን ፡
አልፈልግም ፤ ግን ፡ ልጁን ፡ ወደዚሁ ፡ መምህር ፡ የላከ ፡ ወላጅ ፡
የተገዘተ ፡ ነው ። » ብለው ፡ የልጆቹን ፡ አባቶች ፡ በጠቅላላው ፡
አስረውብኝ ፡ በሚቀጥለው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ማስተምርበት ፡ አዳ
ራሽ ፡ ብሄድ ፡ እንኳንስ ፡ ሊማር ፡ የሚመጣ ፡ በአካባቢውም ፡

የሚሄድ ፡ ልጅ ፡ ጠፋ ። ባርጩማዬ ፡ ላይ ፡ ኩምትር ፡ እንዳልኩ፡ ሳስብ ፡ ሳወጣ ፡ ሳወርድ ፡ እኔን ፡ እንደገሬው ፡ የሚጠቀምብኝ ፡ አሳብ ፡ መጣና ፡ የተማሮቹ ፡ አለመምጣት ፡ እውነትነቱን ፡ አስተባበለልኝ ። እንግዲህ ፡ ተማሪዎቹ ፡ በአዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ አብረውኝ ፡ እያሉ ፡ ዓይኖቼ ፡ ሊያይዋቸው ፡ አልቻሉም ፡ ማለት ፡ ሆነብኝ ። ስለዚህ ፡ ዓይኖቼን ፡ ጠርጥሬ ፡ ልጆቹን ፡ ባሳብ ፡ ብመለከታቸው ፡ በሙሉ ፡ አሉ ። በአሳብ ፡ እያስተማርኩ ፡ በልቼ ፡ ለማደር ፡ የዓይኖቼ ፡ አስተካክሎ ፡ አለማየትን ፡ እንድመርጥ ፡ የውኔ ፡ ቅዠት ፡ አስገደደኝና ፡ « አትንጫጩ ፡ እስኪ ፡ መልእክትን ፡ ድገም ፡ እስኪ ፡ አ — ቡ — ጊ — ዳን ፡ በል ፡ » እያልኩ ፡ ባዶውን ፡ አዳራሽ ፡ አዝ ፡ ጀመር ። በመሀከሉ ፡ አባ ፡ ክንዴ ፡ እክፍል ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ተማሪዎቼ ፡ ሁለተኛ ፡ እንዳይመለሱ ፡ የገዘቱአቸው ፡ መሆኑን ፡ ትዝ ፡ ይለኝና ፡ « ይህስ ፡ ምን ፡ ሆነ ? ግዝቱ ፡ መች ፡ ተፈታ ? ተማሪዎቹስ ፡ በሙሉ ፡ መጥተዋል ፡ ወይ ? እስኪ ፡ ልቁጠራቸው ፡ » እልና ፡ ዓይኖቼን ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ በማስያዝ ፡ በአሳብ ፡ ልጆቹን ፡ ስቆጥራቸው ፡ ልክ ፡ አገኛቸዋለሁ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ክንዴ ፡ ት/ ቤት ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ የበጠበጡኝ ፡ በሕልሜ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ወሰንኩ ። ባንድ ፡ በኩልም ፡ ወኃ ፡ ቀድተው ፡ የሚሰጡኝ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ተገዝተው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የሆዴ ፡ መጉደል ፡ ከዓይኖቼና ፡ ከሌላም ፡ የሰውነት፡ ክፍሎቼ ፡ በልጦ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ የሚያቀርብለትን ፡ አጥቶ ፡ የተቸገረ ፡ መሆኑን ፡ በግብር ፡ ገለጸልኝና ፡ ዓይኖቼን ፡ ዘወርወር ፡ በማድረግ ፡ ሰውነቴን ፡ ሁሉ ፡ አንቅቼ ፡ ብመለከት ፡ ምንም ፡ የለ ። «እንዴ ፡ ይህስ ፡ በሕልሜ ፡ ነው ? ወይስ ፡ በውኔ ? አይ ፡ በሕልሜ ፡ ነው ። ልጆቹ ፡ አሉ ፡ እንደዱሮም ፡ ቀለብ ፡ ይሰፈርልኛል » አልኩ ።

እንደዚህ ፡ ያለ ፡ መጽናኛ ! እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ማስተባበል ! እየተራቡ ፡ ጠግቤአለሁ ፡ ብሎ ፡ ሆድን ፡ መካድ ፡ ሳያዩ ፡ አየሁ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠራቸውን ፡ ዓይኖች ፡ ሥራቸውን፡ እንዳቆሙ ፡ መካድ ፡ በትክክል ፡ የሚያስበውን ፡ አእምሮ ፡



ወደ ፡ አልሆነው ፡ መምራት ፡ ጆሮ ፡ እየሰማ ፡ አልሰማሁም ፡ ማለት ፡ የደም ፡ ሥሮች ፡ ሥራቸውን ፡ በማከናወን ፡ ላይ ፡ እያሉ ፡ ንዝረታቸውን ፡ መካድ ፡ ለኑሮዬ ፡ መፍትሔ ፡ ለችግሬ ፡ መጽናኛ ፡ እንደሆኑ ፡ ቆጥሬ ፡ በርከት ፡ ያሉትን ፡ ቀኖች ፡ አሳለፍኩ ። ሰዓቴን ፡ ሸጬ ፡ ለጥቂት ፡ ቀኖች ፡ ቀለብ ፡ አደረግሁት ።

አባ ፡ ገዘቱብኝና ፡ ሰው ፡ እመንገድም ፡ ሲያየኝ ፡ « ያውልህ ፡ ያ— ሰውዬ ፡ » እያለ ፡ ጣቱን ፡ ይቀስርብኝ ፡ ጀመር ። በሕልሜም ፡ ይሁን ፡ በውኔ ፡ የደረሰብኝ ፡ ተውሳክ ፡ ጸጥታን ፡ ይነሳኝ ፡ ስለነበረ ፡ እንደጋና ፡ እንደዘላን ፡ ሥፍራን ፡ መቀየር ፡ ግዴታ ፡ ሆነብኝ ።

# ኤፍሬም ፡ በነዋሪት ፡ ማርያም ።

እነዋሪት ፡ ማርያም ፡ የምዬ ፡ አባት ፡ አያቴ ፡ የኖሩበትና ፡ ሲሞቱም ፡ የተቀበሩበት ፡ ትልቅ ፡ ደብር ፡ ነው ። ከዜና ፡ ማርቆስ ፡ እንደውሻ ፡ ከተባረርኩ ፡ በኋላ ፡ ወጭ ፡ ወራጁን ፡ እየጠያየቅሁ ፡ በመንዝ ፡ በየመንገዱ ፡ ቀድሞ ፡ ያጠናኋቸውን ፡ የበዓላትን ፡ ስም ፡ እየጠራሁ ፡ በመለመን ፡ በረሃብ ፡ እጅግም ፡ ሳልንገላታ ፡ ፀሐይ ፡ ግን ፡ በጣም ፡ አጠውልጎኝ ፡ ከንፈሮቼ ፡ ውኃ ፡ ለመጠጣት ፡ እንደተዘጋጀ ፡ ኮትቻ ፡ መሬት ፡ ተተርትረው ፡ በአምስተኛው ፡ ቀኔ ፡ እነዋሪት ፡ ማርያም ፡ ደረስኩ ። እነዋሪት ማርያም ፡ በአካባቢው ፡ አያቴ ፡ ይኑሩበት ፡ ሲሞቱም ፡ ይቀበሩበት ፡ እንጂ ፡ የትውልድ ፡ አገራቸው ፡ ባለመሆኑ ፡ እሳቸው ፡ ሲሞቱ ፡ ዘራቸው ፡ የት ፡ እንዳለ ፡ ለማወቅ ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ የሚያሳስብ ፡ ስላልነበረ ፡ « የእገሌ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ » ብዬ ፡ ለመጠጋት ፡ ብሞክር ፡ ተቀባይ ፡ አጣሁ ። ከየሥፍራው ፡ እየተሰበሰቡ ፡ መጥተው ፡ እገዳሙ ፡ ውስጥ ፡ ይኖሩ ፡ ከነበሩት ፡ አካለ ፡ ስንኩሎች ፡ ጋር ፡ ተቀላቅዬ ፡ ለማደር ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ብሄድ ! « አንተ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ነካኝ ፡ ብለህ ፡ ነው ፡ የኛን ፡ ድርጎ ፡ ልትካፈል ፡ የመጣኸው ? ወደል ! ጠብደል » እያሉ ፡ አዋከበውኝ ፡ ከዚያ ፡ እንደውሻ ፡ ተባረርኩ ። የት ፡ ልግባ ? ምን ፡ ዘዴ ፡ ልፍጠር ? ዘዴውማ ፡ እንደልማዴ ፡ በሕልሜ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ሁናቴዬን ፡ መለወጥ ፡ ነዋ ! ዓይኖቼ ፡ እያየ ፡ መካድ ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ሂድ ፡ እየተባልኩና ፡ እየተባረርኩ ፡ ጆሮዎቼ ፡ እንዳልሰሙ ፡ መሆን ፡ እየተወገርኩ ፡ አላመመኝም ፡ ማለትና ፡ መጽናናት ፡ ነዋ ! የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ ፡ ማን ፡ ያገኘዋል ?

በኔ ፡ የደረሰውን ፡ የሕልምና ፡ የውን ፡ መከራ ፡ ተዘርዝሮ ፡ ላንባቢ ፡ ቢቀርብ ፡ ምናልባት ፡ አንባቢዎቹ ፡ የምናነበው ፡ በሕልማችን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኤፍሬም ፡ አልተቸገረም ፡ ብለው ፡ እጥርጥር ፡ ውስጥ ፡ የገቡ ፡ እንደሆነ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ችግሬ ፡ ይህ ፡



ሁሉ ፡ መከራዬና ፡ ስቃዬ ፡ ሳይታወቅልኝ ፡ መቅረቱ ፡ አይደለምን ? በሉ ፡ ይቅር ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ የተራብኩትን ፡ የተጠማሁትን ፡ የታረዝኩትን ፡ የተሰደብኩትን ፡ የተወገርኩትን ፡ ለንባቢ ፡ ገልጬ ፡ የሕልምና ፡ የውኔ ፡ ክርክርም ፡ እዚሁ ፡ ዘርዝሬ ፡ የእኔ ፡ መጠራጠር ፡ ሥር ፡ ሰዶ ፡ አንባቢዎችን ፡ አያስቸግር ። በሉ ፡ ይቅር ፡ እናንተም ፡ ስቃዩን ፡ ባየችሁ ፡ ቁጥር ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ከስቃየ ፡ በዳነ ፡ ብላችሁ ፡ ስለምትመኙ ፡ ምኞታችሁ ፡ እንደኔው ፡ የውን ፡ ሕልም ፡ ሆኖ ፡ እንዲበጠብጣችሁ ፡ አላድርግ ።

በውኔም ፡ ይሁን ፡ በሕልሜ ፡ እንደምረዳው ፡ ከእነዋሪት ፡ ማርያም ፡ ደብር ፡ በኔ ፡ ብጤዎች ፡ ወገራና ፡ ስድብ ፡ እንደውሻ ፡ ተባርሬ ፡ ወጣሁ ። የት ፡ ልሂድ ? መሬቷ ፡ አልቀበል ፡ አለችኝ ፡ ከርስዋ ፡ የተፈጠርሁ ፡ መሆኔን ፡ ካደችኝ ፡ ፍረዱኝ ፡ የት ፡ ልግባ ? ጌታው ፡ ተራው ፡ ሕዝቡ ፡ ለማኙ ፡ ቄሱ ፡ መነኩሴው ፡ ሁሉም ፡ ከኔ ፡ እራቅ ፡ የሚለኝ ፡ ሆነ ። ፍረዱኝ ፡ የት ፡ ልግባ ? ሁሉም ፡ እንደ ፡ ወንጀለኛ ፡ የሚመለከተኝ ፡ ሆነ ፤ መኖሬ ፡ ካልቀረ ፡ መብላት ፡ መኖሬ ፡ ካልቀረ ፡ ለገላዬ ፡ ድሪቶን ፡ መሣይ ፡ ነገር ፡ መኖሬ ፡ ካልቀረ ፡ መኖሪያን ፡ ጎጆ ፡ የሚያስፈልጉኝ ፡ ሆነ ። የደሀ ፡ አመለኞች ፡ አባትና ፡ እናቴ ፡ ሳይቸግራቸው ! ቅርስ ፡ ሳይኖራቸው ፡ ወልደውኝ ፡ እነሱ ፡ ግን ፡ አላፊነታቸውን ፡ በመሸሽ ፡ ከዚህ ፡ አሰቃቂ ፡ ዓለም ፡ ተለዩ ። እኔ ፡ ምን ፡ ልሁን ? የእነሱን ፡ ጽዋ ፡ ለምን ፡ አላገኘውም ? ይኖራል ፡ ተብዬ ፡ እቁጥር ፡ ውስጥ ፡ የምገባ ፡ ሰው ፡ ነኝን ? እንጃ ፡ የእሳትን ፡ መፋጀት ፡ የሚያውቀው ፡ ያው ፡ እሳቱ ፡ የፈጀው ፡ ሰው ፡ ነውና ፡ የኔ ፡ መኖር ፡ ከመኖር ፡ ይቆጠር ፡ እንደሆነ ፡ እኔን ፡ የመሰላችሁ ፡ ተንከራታቾች ፡ ካላችሁ ፡ ፍረዱኝ ። የእኔን ፡ ዓይነት ፡ ዕድል ፡ እጣችሁ ፡ የሆነ ፡ ጉስቁልና ፡ ያጠቃችሁ ፡ ሰዎች ፡ እንዳላችሁ ፡ ፍረዱኝ ! ግን ፡ ምኑን ፡ አውቃችሁ ፡ ትፈርዱኝ ? እናንተ ፡ የእኔው ፡ ብጤ ፡ ሆናችሁ ፡ ምንም ፡ ያላያችሁ ፡ በእኔው ፡ ዓይነት ፡ የተንከራተታችሁ ፡ እንደኔው ፡

ከመኖራችሁ ፡ ያለመኖራችሁን ፡ የምትመርጡ ፡ ከሆናችሁ ፡
ምኑን ፡ አውቃችሁ ፡ ትፈርዱኝ ? ከምንስ ፡ ጋር ፡ የማነጻጸር ፡
ችሎታ ፡ ኖሯችሁ ፡ ታነጻጽሩኝ ? አይሆንም ፡ ካቅማችሁ ፡ በላይ ፡
ነውና ፤ ታዲያስ ? እንዲሁ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ እያልኩ ፡ ራሴን ፡ በራሴ፡
እየደለልኩ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞቴ ፡ ልንከራተት ? አይ ፡ አንተ ፡
አምላክ ! አይ ፡ አንተ ፡ መድኃኒት ፡ ዓለም ! አይ ፡ አንተ ፡
እግዚአብሔር ! አይ ፡ ሦስቱ ፡ ሥላሴዎች ! ምነው ፡ መርዝነቱ ፡
እንደሚፈተን ፡ መድኃኒት ፡ እኔን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ችግር ፡ መፈ
ተኛ ፡ አደረጋችሁኝ ? በሽተኛው ፡ አካለ ፡ ስንኩሉ ፡ አካለ ፡ ጐደ
ሎው ፡ የእናንተን ፡ ስም ፡ እየጠሩ ፡ በልተው ፡ ይኖራሉ ፤ በየቤተ
ክርስቲያኑም ፡ መጠጊያ ፡ አግኝተው ፡ በረንዳ ፡ ላይ ፡ ተኝተው ፡
ያድራሉ ፤ የመጀመሪያ ፡ ምጽዋት ፡ ተቀባዮችም ፡ ናቸው ።
እኔሳ ! እኔማ ፡ አካለ ፡ ስንኩልነቴ ፡ ባንድ ፡ የሰውነት ፡ ክፍል ፡
ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሰው ፡ ያላወቀልኝና ፡ ያላዘነልኝ ፡ ሙሉ ፡ አካለ ፡
ስንኩል ፡ ነኛ ! ታዲያ ፡ በዚህ ፡ አንተ ፡ አምላክ ፡ ትደሰታለህን ?
ሁሉንም ፡ የምትችል ፡ ነህ ፤ ይህ ፡ ከሆነ ፡ እኔን ፡ ከማጎሳቆል ፡
ሌላ ፡ መደሰቻ ፡ ልትፈጥር ፡ ትችል ፡ የለምን ? መቼም ፡ የምታ
ውቅ ፡ ብትሆን ፡ ገና ፡ ሳልፈጠር ፡ የምትራራ ፡ ብትሆን ፡ ገና ፡
ሳልቸገር ፡ ሁሉንም ፡ ልታስተካክልኝ ፡ ትችል ፡ ነበር ። ግን ፡
በማን ፡ ዳኝነት ! በማን ፡ አስገዳጅነት ! እናትህ ፡ ማርያምም ፡
ብትሆን ፡ በአማላጅነት ፡ በቀር ፡ በዳኝነት ፡ አታይብህ ! ምን ፡
አለ ፡ » እያልኩ ፡ ምርር ፡ ብዬ ፡ በማልቀስ ፡ አቅጣጫ ፡ የሌ
ለው ፡ ጉዞዬን ፡ ቀጠልኩ ። ዳገቱን ፡ ቁልቁለቱን ፡ ወጥቼ ፡
ስወርድ ፡ ውዬ ፡ ካደርኩ ፡ በኋላ ፡ ደክሞኝ ፡ አንድ ፡ ዝግባ ፡ ሥር ፡
አረፍኩ ። ጊዜው ፡ በግምት ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ይሆናል ።

«አንተ ፡ ዛፍ ! ምነው ፡ ግንድህ ፡ ይሻክራል ? ቅርንጫፎ
ችህ ፡ ይልቅ ፡ ይለሰልሳሉ ፤ አበባው ፡ ለነገ ፡ ፍሬ ፡ የሚሆን ፡ ይመ
ስላል ፤ ጥሩ ፡ ተስፋ ፡ ነው ።



የሥሮችህን ፡ ግን ፡ ማን ፡ ያውቃል ? አፈር ፡ ለብሰዋልና ፡ »
እያልኩ ፡ የተደገፍኩትን ፡ ዝግባ ፡ ግንድ ፡ እደባብሰው ፡ ስለነ
በር ፡ አሁን ፡ ሳስበው ፡ መልሶ ፡ ይደንቀኛል ።

ግንዱን ፡ ያሻከረው ፡ ቅጠሎቹን ፡ ያለሰለሰው ፡ አበባዎቹ ፡
ለዓይን ፡ አስደሳች ፡ እንዲመስሉ ፡ ያደረጋቸው ፡ ሥሮቹን ፡
አፈር ፡ ውስጥ ፡ ቀብሮ ፡ የመሬቷን ፡ ቅባት ፡ እንዲመጡለት ፡
የሰደደው ፡ የራሱ ፡ ፍላጐት ፡ ሳይሆን ፡ የዛፎች ፡ የተፈጥሮ ፡
ጠባይ ፡ መሆኑን ፡ ለምን ፡ አልተረዳሁ ? እውነትም ፡ የሚደ
ንቅ ፡ ነው ።

እዚያቹ ፡ እንዳለሁ ፡ አንድ ፡ የአገልግል ፡ ምግብ ፡ የያዙ ፡ መን
ገደኛ ፡ ጥላው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ሊበሉ ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ አገልግ
ሉን ፡ ከፈታቱ ፡ በኋላ ፡ « አንተ ፡ ልጅ ፡ እዚያ ፡ ወሃ ፡ አለልህ ፡
ቶሎ ፡ እጅህን ፡ ታጠብና ፡ አብረኸኝ ፡ ብላ ፡ » ሲሉ ፡ አይቼው ፡
የማላውቀውን ፡ ዓይነት ፡ ከፍተኛ ፡ ምጽዋት ፡ አደረጉልኝና ፡
ቶሎ ፡ ታጥቤ ፡ ቀረብኩ ። አዬ ፡ ከዚያ ፡ በኋላማ ፡ ምን ፡ ልን
ገራችሁ ! የእንጀራው ፡ ባለቤት ፡ አንዴ ፡ ሲጐርርሱ ፡ እኔ ፡
ሁለቱን ፡ ጉርሻ ፡ አጣጥሜ ፡ ለሦስተኛው ፡ እቀራረባለሁ ፤ አን
ስቶ ፡ መዋጥን ፡ እንጂ ፡ ማኘክና ፡ ማጣጣም ፡ ከቶም ፡ አልሞ
ከርኩ ። ሰውዬው ፡ የኔን ፡ መንገብገብ ፡ አይተው ፡ ችግሬን ፡
በመጠኑ ፡ ሳይረዱልኝ ፡ አልቀሩም ። «አንተ ፡ ብላ ፡ አይዞህ ፡ »
እያሉኝ ፡ ለሦስት ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ሊጠቀሙበት ፡ የያዙትን ፡
ምግብ ፡ አንዲት ፡ ፍርፋሪ ፡ ሳትቀረኝ ፡ አገልግሉን ፡ አራግፌ ፡
መለስኩላቸው ። «ጌታዬ ፡ ውለታዎን ፡ የሚመጥን ፡ የምስጋና ፡
ቃል ፡ ላገኝ ፡ አልችልምና ፡ በደፈናው ፡ መላሴና ፡ የበላው ፡
ሆዴ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡ የወለዱት ፡ ይባረክ ፡ የያ
ዙት ፡ ይበርክት ፡ ትውልድዎን ፡ ከመባከንና ፡ ከመንከራተት ፡
ያድንልዎ ፡ ይላሉ ። ሞት ፡ የጠላኝ ፡ ምድር ፡ የካደችኝ ፡ ፍጡር ፡
ሦስት ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ሕይወቴን ፡ ልትጠብቅልኝ ፡ የምትችል ፡
እንጀራ ፡ አበሉኝ ። አሁንም ፡ ለደግነት ፡ ወሰን ፡ የለውምና ፡

እግዚአብሔር ፡ ይስማዎት ፡ እንደሆን ፡ ተስፋ ፡ እንዳላጣ ፡ ምድ
ሪቱ ፡ እንዳትክደኝ ፡ መጠጊያ ፡ እንዳገኝ ፡ እንዲያደርግልኝ ፡
ይጸልዩልኝ» እያልኩ ፡ በማስተዛዘን ፡ ምስጋናና ፡ ልመና ፡ አንድ፡
ላይ ፡ በማሰማት ፡ ላይ ፡ እያለሁ ፡ ልማደኛው ፡ እንባዬ ፡ ያቀርር ፡
ጀመር ።

ሰውዬው ፡ ለለቅሶ ፡ የተዘጋጁትን ፡ ዓይኖቼን ፡ አይተው ፡
በኃይል ፡ ተገረሙ ፤ ሰው ፡ ሲርበው ፡ ማልቀስ ፡ ሲጠግብ ፡
መሳቅ ፡ እንጂ ፡ ያን ፡ ያህል ፡ ምግብ ፡ እንዳሳማ ፡ ጥርግርግ ፡
ካደረግ ፡ በኋላ ፡ የተራበ ፡ መስሎ ፡ የሚያለቅስ ፡ ፍጡር ፡ ትክክ
ለኛ ፡ ሰው ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡ በሚባለው ፡ መጠንም ፡ ሰው
ነቱ ፡ ላይ ፡ አይታይም ፡ በሚል ፡ ተገርመው ፡ ከእግር ፡ እስከራሴ ፡
ከተመለከቱኝ ፡ በኋላ ፡ « ምን ፡ ሆንክ ? ከየትስ ፡ ተነስተህ ፡
ወዴት ፡ ትሄዳለህ ? » ሲሉ ፡ ጠየቁኝ ፡ እኔም ፡ አባቴ ፡
ጦር ፡ ሜዳ ፡ ከሄደበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ እስከሞተበት ፡ ጊዜ ፡
የነበረውን ፡ የእምዬና ፡ የእኔ ፡ የኑሮ ፡ ሁናቴ ፡ በኋላም ፡ የእምዬ ፡
ችግርና ፡ በሞት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ መለየት ፡ ቀጥሎም ፡ ምድሪቱ፡
እኔን ፡ ክዳኝ ፡ ባንድ ፡ ሥፍራ ፡ ስቀመጥ ፡ የከበድኳት ፡ ይመ
ስል ፡ የምታባርረኝ ፡ በየቦታው ፡ እንደ ፡ ወንጀለኛ ፡ የምታስወግ
ረኝ ፡ በመሆኔ ፡ ቅርስ ፡ የሌለው ፡ ዘላንነቴ ፡ አስለቅሶኝ ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ ከበላሁ ፡ በኋላ ፡ መደሰት ፤ ከጠገብኩ ፡ በኋላ ፡ መሳቅ ፡
እንደነበረብኝ ፡ ሕዋሳቶቼም ፡ ሊመሰክሩ ፡ በቻሉ ። ጌታዬ ፡
አሁን ፡ ያበሉኝ ፡ ዓይነት ፡ ምግብ ፡ ቀርቶ ፡ ፍርፋሪ ፡
እንኳን ፡ አነሰኝ ፡ ሳልል ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገንኩ ፡
በኖርኩ ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ እሠራለሁ ፡ ብል ፡ እንቅፋቱ ፡ እየበረከተ !
የሚረዱኝ ፡ ሁሉ ፡ እየተገዘቱ ! ከሰው ፡ ጋር ፡ እንዳልቀላቀል ፡
እያደረጉኝና ፡ እያስወገሩኝ ፡ ብቻ ፡ እንዳበደች ፡ ውሻ ፡ አንዱ ፡ አባሮ ፡
ላንዱ ! አንደኛው ፡ ተቀብሎ ፡ ለሌላው ፡ እያሳለፉኝ ፡ በጭንቅና ፡
በመከራ ፡ የኖርኩ ፡ እንዲሁ ፡ በሰው ፡ ደረጃ ፡ የምቆጠር ፡ ዕድለ ፡
ስንኩል ፡ ሰው ፡ ስለሆንኩ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ ብዬ ፡ ለማውራት ፡ እን
ኳን ፡ የማልደፍር ! የምጠራጠር ! ወገንና ፡ ዘመድ ፡ ቀርቶ ፡



እግዚአብሔር ፡ ራሱ ፡ የራቀኝ ፡ ልዩ ፡ የሆንኩ ፡ ፍጡር ፡ ነኝ »
ስላቸው ፡ ለልፍለፋዬ ፡ አንድም ፡ መልስ ፡ ሳይሰጡኝ ፡ « መሸ
ቶአልና ፡ ደህና ፡ ሁን ! ይቅናህ » ብለውኝ ፡ ብድግ ፡ አሉ ። ደነ
ገጥኩ ! ምን ፡ አስቀይሜአቸው ፡ ይሆን ፡ ብዬ ፡ ተሸበርኩ ።
በኋላ ፡ ግን ፡ « አዬ ፡ አምላኬ ፡ እባክህ ፡ ግዝቱ ፡ እኔ ፡ ላይ ፡ እን
ዳይደርስ ፡ አድርግ ! እባክህን ፡ ማረኝ ፡ ተለመነኝ ፡ የሚረዱኝ ፡
ሁሉ ፡ ተገዘቱ ፡ የሚለው ፡ እኮ ፡ ሃይማኖትን ፡ የሚቃወም ፡ ባህ
ልን ፡ የሚያበላሽ ፡ አንድ ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ቢሠራ ፡ ነው ፡ »
እያሉ ፡ ሲያጉረመርሙ ፡ ሰማሁና ፡ « አየ ፡ የሰውየው ፡ ሁኔታ ፡
እንደዚህ ፡ መሆኑ ፡ ካልቀረ ፡ እንኳንም ፡ ከበላሁ ፡ በኋላ ፡ ሆነ ፡
እንኳንም ፡ ሳልበላ ፡ አልለፈለፍኩ ፡ » እዚያው ፡ እንደተቀመጥኩ
እግዚአብሔር ፡ ያለበትን ፡ ሳላውቅ ፡ ፊቴን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡
አዙሬ ፡ አንገቴን ፡ ቀና ፡ በማድረግ ፡ « አንተ ፡ አምላክ ፡ » እለ
ው ፡ ጀመር ። « ለካስ ፡ ስትፈልግ ፡ ማብላትም ፡ ታውቃለህ ?
ለካስ ፡ ፈቃድህ ፡ ከሆነ ፡ ከየትም ፡ ታዝዛለህ ? ታዲያ ፡ ቸርነትህ ፡
ለምን ፡ ወሰን ፡ ታበጅለታለህ ? አሁን ፡ እኔ ፡ በማላውቀው ፡
አገር ፡ በዚህ ፡ ዝግባ ፡ ሥር ፡ ለምን ፡ ግራ ፡ ይግባኝ ? ምግብ ፡ አዘ
ዝክልኝ ፡ በላሁ ፡ » ስል ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደሰማኝ ፡ ከቆጠ
ርኩት ፡ በኋላ ፡ አንገቴን ፡ መለስ ፡ አድርጌና ፡ ዝግባውን ፡ ተደ
ግፌ ፡ ቁጭ ፡ አልኩ ። ዝግባው ፡ እጉዳና ፡ መሀል ፡ ስለነበረ ፡
ሰው ፡ ሲያልፍ ፡ አግኝቼ ፡ አሳድሩኝ ፡ እንድል ፡ ነበር ፡ የተቀመ
ጥኩት ፡ ግን ፡ የኔን ፡ ሕይወት ፡ የማይቃወም ፡ ነገር ፡ የለምና ፡
እንቅልፍ ፡ እንደውኃ ፡ ሙላት ፡ መጥቶ ፡ ይዞኝ ፡ እልም ፡ አለ ።

እንደተጋደምኩ ፡ ሕልሜ ፡ በአጀብ ፡ መጣና ፡ የተደገፍ
ኩት ፡ ዝግባ ፡ ዜና ፡ ማርቆስ ፡ ገዳም ፡ አካባቢ ፡ ሳስተምር ፡ ባላ
ባቱ ፡ ያበረከቱልኝ ፡ ባርጩማ ፡ መስሎኝ ፡ የዛፎች ፡ በነፋስ ፡
ኃይል ፡ መወዛወዝ ፡ ድምፅ ፡ ይሰጥ ፡ ስለነበረ ፡ የተማሪዎቼ ፡
ጫጫታ ፡ መስሎኝ ፡ « ዝም ፡ በሉ ፡ አትንጫጩ » ብዬ ፡ ጸጥ
ታን ፡ እየተጠባበቅሁ « መልክተ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐዋርያ ፡ ወልደ ፡
ዘብዴዎስ ፡ » እያልኩ ፡ እመራ ፡ ጀመር ። እዚያቹ ፡ ባርጩማ ፡

ላይ ፡ ተቀምጬ ፡ እያስተማርኩ ፡ የመጀመሪያው ፡ የማስተማ ሪያ ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፡ ያልቅና ፡ የሰውነትን ፡ ማጠንከሪያ ፡ ትምህ ሀርት ፡ ለማስጠናት ፡ ይዣቸው ፡ ወደውጭ ፡ ለመውጣት ፡ እን ደተዘጋጀሁ ፡ ድንገት ፡ አንድ ፡ ፈረሰኛ ፡ እየጋለበ ፡ አለፈና ፡ በኮቴው ፡ ድምፅ ፡ ከተጋደምኩበት ፡ ነቃሁ ። ስነቃ ፡ ያለሁት ፡ በማላውቀው ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ በማላውቀው ፡ መንደር ፡ እዚያች ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ መሆኔን ፡ ተረዳሁ ። ሕልሜን ፡ ወደማሰላሰሉ ፡ ስል ፡ የውኔ ፡ ቅዠት ፡ ከተፍ ፡ እያለ ፡ አስቸገረኝ ። ጊዜውም ፡ ወደመ ምሽት ፡ ብሏል ።

በአሳብ ፡ ስጨነቅና ፡ ስተራመስ ፡ ጥቂት ፡ እንደቆየሁ ፡ ወደ ፡ ፍንክች ፡ ከተማ ፡ የሚሄዱ ፡ ሦስት ፡ ፋኖችን ፡ አገ ኘሁ ። ከሦስቱ ፡ ፋኖዎች ፡ አንደኛው ፡ ቀድሞ ፡ ተማሪ ፡ በነበርኩበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ አቤቱታ ፡ ስለነበረው ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፌለት ፡ «ውለታህን ፡ ለመክፈል ፡ ያብቃኝ ፡ » ብሎኝ ፡ የነ በረ ፡ ስሙን ፡ የማላውቀው ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ አገኘሁትና ፡ « ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ ጌታዬ ፡ » አልኩት ፡ እሱን ፡ በተለይ ፤ እሱም ፡ በጊዜው ፡ በነበረኝ ፡ መልክ ፡ ሊለየኝ ፡ ባለመቻሉ ፡ በቀላሉ ፡ « እንዴት ፡ ዋልክ ፡ » አለኝ ፤ መለስኩና ፡ « ጌታዬ ! ዘንግተው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በፍንክች ፡ ከተማ ፡ በ፲፱፻፴፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ - - - - - - » በማለት ፡ ቀኑንና ፡ ሰዓቱን ፡ ሥፍራውን ፡ የጻፍኩለትን ፡ ጉዳይና ፡ አድራሻውን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ገልጬ ፡ ስነግረው ፡ « አይደረግም ! አይደረግም ! » አለ ፡ ደጋግሞ ። እኔም ፡ « ጌታዬ፡ ያለዎት ፡ ሰብአዊ ፡ ርኅራኄ ፡ እንዲገረሙና ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ እንዳይመስልዎ ፡ አደረገዎ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ እኔው ፡ ነኝ ፤ ዓይኖች ዎን ፡ አይጠርጥሩ ፤ ያመለከትክዎት ፡ ምልክቶችንም ፡ አይካዱ ፤ ውለታህን ፡ ለመክፈል ፡ ያበቃኝ ፡ ብለው ፡ ስለነበረ ፡ እነሆ ፡ ፈጣሪ ፡ አምላኬ ፡ በችግሬ ፡ ቀን ፡ እርስዎን ፡ አምጥቶ ፡ አገና ኘኝ ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ካለሁቦት ፡ ከጭለማ ፡ ቦታ ፡ ከማላው ቀው ፡ ቀበሌ ፡ ወደ ፡ ፍንክች ፡ ከተማ ፡ ከእናንተው ፡ ጋር ፡ ውሰ ዱኝ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ባላሰበው ፡ ጊዜ ፡ አገናኝቶ ፡ ውለ



ታውን ፡ እንዲመልስ ፡ ስለሚያደርግ ፡ ዛሬ ፡ ለምታደርጉልኝ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ወደፊት ፡ ውለታችሁን ፡ እመልስ ፡ ይሆናል ። ፈቃደኝነት ፡ ሳያንሰኝ ፡ አቅም ፡ ባጣም ፡ ውለታችሁን ፡ እግ አብሔር ፡ ይከፍላችኋልና ፡ እዚህ ፡ እንደ ፡ ጥንብ ፡ ጥላችሁኝ ፡ አትሂዱ ፡ ዛሬ ፡ ዓይኖቼ ፡ እያዩ ፡ የጅብ ፡ እራት ፡ ልሆን ፡ ነው ፤ » ብዬ ፡ አለቀስኩባቸውና ፡ ያ ፡ ውለታ ፡ እንዲከፍለኝ ፡ የተመኘ ልኝ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሁሉም ፡ አዝነውልኝ ፡ « በልና ፡ አይዞህ ! አዋጥተን ፡ እናሳፍርሃለን ፡ » ብለውኝ ፡ አብሬአቸው ፡ ተጓዝኩ ። ጨረቃዋ ፡ የፀሐይን ፡ ብርሃን ፡ እያንጸባረቀችልን ፡ ኮከቦች ፡ የሙነመነ ፡ ተስፋ ፡ የመሰለውን ፡ ብርሃናቸውን ፡ እየላኩልን ፡ በተጨማሪም ፡ በባትሪ ፡ እየተረዳን ፡ የንግድ ፡ መኪናዎች ፡ ወደሚገኙበት ፡ ወደ ፡ ፋካ ፡ ደረስን ። ጊዜው ፡ ከምሽቱ ፡ አምስት ፡ ሰዓት ፡ ሆኖ ፡ ስለነበረ ፡ እዚያው ፡ አድረን ፡ ጠዋት ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ያ ፡ የማውቀው ፡ ሰውዬ ፡ ሁለት ፡ ብር ፡ ግን ፡ እነዚያ ፡ ፋኖዎች ፡ በድምሩ ፡ ሰባት ፡ ብር ፡ ለባለመኪናው ፡ ከፍለውልኝ ፡ ጉዞአችንን ፡ ቀጠልን ። እንደ ዚያ ፡ መንሳቆሌንና ፡ ባላገርም ፡ ለምን ፡ እንደሄድኩ ፡ በተራ ፡ እየጠየቁኝና ፡ የደረሰብኝን ፡ መከራ ፡ ዘርዝሬ ፡ እየነገርኳቸው ፤ ወደ ፡ ፍንክች ፡ ከተማ ፡ ደረስን ። «የምታውቀው ፡ አለህን ? » አለኝ ፡ አንዱ ፤ እኔም ፡ « አዎን ፡ ከእንግዲህ ፡ አላስቸግራች ሁም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡ » ብያቸው ፡ ስንለያይ ፡ ቀድሞ ፡ አውቀው ፡ የነበረው ፡ ሰውዬ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ አውጥቶ ፡ ሰጠኝና ፡ ተሰናብቻቸው ፡ ሄድኩ ። ጊዜው ፡ ከምሽቱ ፡ ወደ ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ ተቀራርቦ ፡ ስለነበረ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ የእህል ፡ በረንዳ ፡ ሔጄ ፡ ተኛሁ ። በማግሥቱ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ሥራን ፡ ሠርቼ ፡ ሆዴን ፡ ማሸነፍ ፡ እንደምችል ፡ ማሰላሰል ፡ ውስጥ ፡ ገባሁና ፡ ላመል ፡ እንኳን ፡ እንቅልፍ ፡ ሳይወስደኝ ፡ የበረንዳው ፡ ውርጭ ፡ ሲገርፈኝ ፡ ሰውነቴ ፡ ሲንቀጠቀጥ ፡ « በዚህ ፡ ወጥቶ ፡ በዚህ ፡ ወርዶ » እያልኩ ፡ ትርኪ ፡ ምርኪውን ፡ አእምሮዬ ፡ ውስጥ ፡ ሳብሰለስል ፡ ያጠናሁት ፡ የልመና ፡ ዘዴ ፡ ትዝ ፡

አለኝ ። «እንዲያ ! ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ ዘዴ ፡ ምን ፡ አለኝ ? ባንድ ፡ ልደታ ፣ በሁለት ፡ ሩፋዬል ፡ በሦስት በዓታ - - - » እያልኩ ፡ ለማስታወስ ፡ ብሞክር ፡ ልክ ፡ ነኝ ። ነገሩስ ፡ አልነበረም ።

በማግሥቱ ፣ ገና ፡ ወፍ ፡ ጭው ፡ ሳይል ፡ ተነሳሁና ፡ ሌሎች ፡ የኔ ፡ ብጤዎች ፡ ያልነበሩበትን ፡ አንዲት ፡ ጥግ ፡ ይዤ ፡ ድምጼን ፡ በጣም ፡ ለሰስ ፡ በማድረግ ፡ ሰው ፡ ሲያልፍም ፡ ሆነ ፡ ማንም ሳይኖር ፡ « ስለ ፡ ሩፋኤል ! ስለ ፡ ሩፋኤል ! ስለ-ሩፋኤል ! » እያልኩ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ በመላስ ፡ ሥራ ፡ ዋልኩና ፡ አሥር ፡ ሳንቲም ፡ ብቻ ፡ አገኘሁ ። ቀኑ ፡ መስሎኝ ፡ ሩፋኤል ፡ ስል ፡ ዋልኩ ፡ እንጂ ፡ ለካስ ፡ ስለበዓታ ፡ እያልኩ ፡ መለመን ፡ ነበረብኝ ! አይ ፡ ጉድ ፣ ያለ ፡ ሥራዩ ፡ ገብቼ ፡ ሩፋኤልን ፡ ያለቀኑ ፡ ሳነግሰው ፡ ወጭ ፡ ወራጁ ፡ እንዴት ፡ ታዝቦኝ ፡ ይሆን ? መሸና ፡ ያቺን ፡ አሥር ፡ ሳንቲሜን ፡ ይዤ ፡ አንድ ፡ እንጀራ ፡ ለመብላት ፡ ወደ ፡ ሆቴል ፡ ቤት ፡ ሄድኩ ። አንድዋን ፡ እንጀራ ፡ ስበላ ፡ በፍጹም ፡ ሆዴ ፡ ውስጥ ፡ ጠብ ፡ ያለ ፡ ስላልመሰለኝ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ካመጡኝ ፡ ሰዎች ፡ አግኝቼ ፡ የነበረውን ፡ ብር ፡ መንዝሬ ፡ አንድ ፡ እንጀራ ፡ ጨመርኩና ፡ አምላኬን ፡ ተመስገን ፡ እለው ፡ ጀመር ። እዛቹ ፡ እንደተቀመጥኩ ፣ እንቅልፍ ፡ ሸለብ ፡ ሊያደርገኝ ፡ ሞከረና ፡ ተነስቼ ፡ ወጣሁ ። ከዚያ ፡ በኋላማ ፡ ምኑ ፡ ቅጡ ፡ የልመና ፡ ሥራ ፡ ገና ፡ ያልሰለጠንኩበት ፡ መሆኑን ፡ ተገነዘብኩ ፤ ችግሬም ፡ ሥር ፡ ሰዷል ።



# አያቴና ፡ እኔ ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ጠዋት ፣ ክንቸር ፡ ሰፈር ፡ ጥጉን ፡ ይዤ ፣ ጭብጥብጥ ፡ ብዬ ፣ « ስለ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ! ስለ ፡ እዛኝቱ ፡ ማርያም ! » እያልኩ ፡ ዓይኖቼን ፡ ከወጪና ፡ ከወራጁ ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ ሳንከራትት ፡ የሁለት ፡ ዕድለ ፡ ቢሶች ፡ ወላጅ ፡ አያቴ ፡ ራሳቸውን ፡ እማሆይ ፡ አሰኝተው ፣ አንዲት ፡ በማደፏ ፡ ምክንያት ፡ ቀለሟ ፡ የማይታወቅ ፡ ቆባቸውን ፡ ደፍተው ፣ አንካሴአቸውን ፡ በሦስተኛ ፡ ደረጃ ፡ የእግሮቻቸው ፡ ረዳት ፡ አድርገው ፣ ወልገድ ፡ ወልገድ ፡ ሲሉ ፡ እግሮቻቸውን ፡ እያጋጩ ፡ አጠገቤ ፡ መጡና ፡ ቆም ፡ ብለው ፡ ከያዝዋት ፡ ትንሽ ፡ አቅማዳ ፡ ጥቂት ፡ ሽንብራ ፡ ዘገን ፡ አድርገው ፡ «እንካ» አሉኝ ። ሰውነቴ ፡ ሰንጠቅ ፡ አለ ። ፊት ፡ ፊታቸውን ፡ እያየሁ ፡ ሽንብራውን ፡ ልቀበላቸው ፡ ስል ፡ እጆቼ ፡ እንዲቀበሉ ፡ የሰደድኳቸው ፡ ያለቦታው ፡ ኖሮ ፡ ሽምብራው ፡ ፈሰሰ ። እማሆይ ፡ ግራ ፡ ገባቸው ፣ የለማኝ ፡ ተንቀባራሪና ፡ የሚሰጠውን ፡ ምጽዋት ፡ አጥብቆ ፡ የማይዝ ፡ ከየት ፡ መጣ ፡ ብለው ፡ የተገረሙ ፡ ለመሆናቸው ፡ በፊታቸው ፡ ይነበብ ፡ ነበር ። እማሆይ ፡ ሁለቱ ፡ የፊት ፡ ጥርሶቻቸው ፡ ተነቅለው ፣ ፊታቸው ፡ ልክ ፡ የሸንፍላን ፡ መልክና ፡ ጠባይ ፡ የያዘ ፡ መስሎ ፣ ጸጉራቸው ፡ ሊቆጠር ፡ በሚችል ፡ ዓይነት ፡ በኖ ፡ አልቆ ፣ ዓይኖቻቸው ፡ የማየት ፡ ኃይላቸው ፡ ደክሞ ፡ ሳያቸው ፣ ከእግር ፡ ጥፍሮቼ ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ እራሴ ፡ ድረስ ፡ ከውስጥ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ረመጥ ፡ ይፈጀኝ ፡ ጀመር ። እንባዬን ፡ ማፍሰስ ፡ ቀጠልኩ ። እማሆይም ፡ ግራ ፡ ሲገባቸው ፡ « ምነው ፡ አንተ ፡ ሰው ! ያምሃል ? » ሲሉ ፡ ጠየቁኝ ። እኔም ፡ «እማሆይ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ብለው ፡ ለትንሽ ፡ ጊዜ ፡ እዚሁ ፡ ይጠብቁኝ ፣ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚነሳብኝ ፡ የሚያስለቅስ ፡ በሽታ ፡ አለብኝ » ስላቸው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ጠርቼባቸዋለሁና ፡ እዚያቹ ፡ ቁጭ ፡ አሉ ። እኔም ፡ እስኪወጣልኝ ፡ ድረስ ፡ እንባዬን ፡ አነባሁና ፡ ሲያልቅብኝ ፡ ዓይኖቼን ፡ በጨርቄ ፡ ጠራረግሁ ። እማሆይ ፡

እኔን ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ይዛመደኛል ፡ ብለው ፡ አልጠረጠ
ሩኝም ። እኔም ፡ እንዲያውቁኝ ፡ አልፈለግሁምና ፡ መላልሼ ፡
ጐንደሬ ፡ እንደሆንኩ ፡ የሚያሳምናቸውን ፡ አነጋገር ፡ ካሰማኋ
ቸው ፡ በኋላ ፡ ከወዴት ፡ እንደመጡ ፡ ልጠይቃቸው ፡ ፈለግሁ ።
ስላደረጉልኝ ፡ ምጽዋትና ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ስላስለቀሱኝ ፡ ምስ
ጋናዬን ፡ ደረደርኩላቸውና ፡ ስማቸውን ፡ ብጠይቃቸው ፡ « እማ
ሆይ ፡ ወለተ ፡ ወልድ ፡ እባላለሁ ፡ » ሲሉ ፡ መለሱልኝ ። ያለቀው ፡
እንባዬ ፡ ከየት ፡ ተተክቶ ፡ እንዴት ፡ እንደወረደ ፡ ሳላውቅ ፡ ጉል
በቴ ፡ ላይ ፡ ይንጠባጠብ ፡ ጀመር ። « የተወለድኩትም ፡ ሆነ ፡
የኖርኩት ፡ እፍንክች ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ሳይሆን ፡ በመጀመሪያ ፡
ገላዬ ፡ ከሚባል ፡ ባለቤቴ ፡ ጋር ፡ ከጐንቴ ፡ ተሰደን ፡ ወደ ፡ እነ
ዋሪት ፡ ማርያም ፡ ሄድንና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ወለድን ፤
ከዚያም ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ባሌን ፡ ተነጠኩና ፡ እነዋሪ ፡
ማርያም ፡ ውስጥ ፡ የሚያስጠጋኝን ፡ ሰው ፡ አጥቼ ፡ ወደ ፡ ገደባኖ ፡
ሄድኩ ፡ » ብለው ፡ ሲመልሱልኝ ፡ « ገደባኖ ፡ ውስጥ ፡ ዘመድ ፡
ነበረዎትን » ብላቸው ፡ « አዎን ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ ወልዳ ፡
በሞት ፡ የተለየችኝ ፡ ልጄ ፡ ያገባችው ፡ የዚያ ፡ አገር ፡ ሰው ፡
ነበርና ፡ እስዋን ፡ ተከትዬ ፡ ሄጄ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህች ፡
ልጄም ፡ በበኩሏ ፡ እንደኔ ፡ ገና ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ እንደወለደች ፡
ሳትደግም ፡ ባልዋ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ሄዶ ፡ ለሀገሩ ፡ እንዲሞት ፡
ተደረገና ፡ እሱም በሰው ፡ አገር ፡ በኤህ ፡ ወደቀ ፡ ሳይባል
ሞቶ ፡ አሞራ ፡ በላው ፡ ከያ ፡ ወዲያ ፡ ልጄ ፡ የዓይኔ ፡ አበባ ፡
ሳይቸግራት ልጅዋን ፡ ዳዊት ፡ ይድገም ፡ ብላ ፡ ባላባቱን ወተ
ወተችና ፡ ባላባቱም ፡ ለመንግሥት ፡ ወስዶ ፡ አቀበለላት ።
እስዋ ፡ ለብቻዋ ፡ ያለ ፡ እርዳታ ፡ በችግር ፡ ስትማቅቅ ፡ የቁም ፡
ስቃይዋን ፡ ካየች ፡ በኋላ ፡ ታመመችና ፡ ተነጠለችበኝ ። አይ !
ምነው ፡ እባክህን ፡ አንተ ፡ ሰው ! ለምን ፡ ቁስሌን ፡ ነካህብኝ ?
እረ ፡ ተወኝ ፡ » እያሉ ፡ ኃይላቸው ፡ ጨርሶ ፡ ከደከመው ፡ ዓይ
ናቸው ፡ እንባቸው ፡ ቡልቅ ፡ ቡልቅ ፡ ሲያደርጉት ፡ በለቅሶው ፡
ላጅባቸው ፡ ተገደድኩ ። እማሆይም ፡ እኔ ፡ ሳለቅስ ፡ የርኅራሄ



ነት ፡ መሰላቸው ፡ እንጂ ፡ የእሳቸው ፡ ቁስልና ፡ የኔ ፡ ቁስል ፡
የተመሳሰለ ፡ መሆኑን ፡ ጭራሽ ፡ አልጠረጠሩኝም ። « በኋላስ ፡
እንዴት ፡ ሆነ ? ልጇስ ፡ የት ፡ ደረሰ ? እርሶስ ፡ እንዴት ፡ ብለው ፡
ለብቻዎ ፡ ኖሩ ? » ስል ፡ ጠየቅኋቸውና ፡ « አዬ ፡ ልጄ ፡ ምኑን ፡
ነግሬህ ፡ ምኑን ፡ ልዘልቀው ! ስለእኔ ፡ ኑሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ያለ ፡ ሰው ፡ አንዳንዱ ፡ የምለብሰውን ፡ ጨርቅ ፡ ሌላው ፡ የሆ
ዴን ፡ ችግር ፡ እያቃለለልኝ ፡ ይኸውና ፡ እስካሁን ፡ ቆየሁ ፤
እኔ ፡ እንዲያውም ፡ ግደለኝ ፡ ብለው ፡ አልቀበልሽ ፡ አለኝ ፡
እንጂ ፡ ረፍት ፡ የፈለግሁት ፡ ገና ፡ ልጄ ፡ ከኔ ፡ እንደተለየች ፡
ነበር ። ሥቃይሽን ፡ እዚች ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ ጨርሺ ፡ ብሎኝ ፡
ይኸውና ፡ እሰቃያለሁ ። ልጄ ፡ እንደታመመች ፡ «ልጄን ፡ አምጥ
ታችሁ ፡ አሳዩኝ ! እኔ ፡ እችን ፡ ወር ፡ አላልፋትም»፡ ብላ ፡ አስቸ
ገረችንና ፡ ለትምህርት ፡ የሄደው ፡ ልጇችን ፡ ተልኮበት ፡ መጥቶ ፡
ሳትሞት ፡ ደርሶባት ፡ በሕይወት ፡ ከተለቃቀሱ ፡ በ ፡ - - በ - -
በኋ - - ኋላ ፡ ሕይወቷ ፡ አልፎ ፡ አብረን ፡ ቀበርናት ። እሱም ፡
እስከ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ከኔው ፡ ጋር ፡ ቆይቶ ፡ ተነስቶ ፡
ሄደ ። ይኸውና ፡ አሥር ፡ ዓመቴ ፡ ታየሁት ፡ » እያሉ ፡ ማልቀስ ፡
ሲጀምሩ ፡ እኔም ፡ አጀብኋቸውና ፡ አሁንም ፡ እንባችንን ፡ ቀነ
ስን ፡ « በዙ ፡ ትምህርት ፡ ተምሮ ፡ ዳዊት ፡ ጨርሶ ፡ ጥበበኛ ፡
ሆነ ፡ መንግሥትም ፡ ወደደው ፡ ብለው ፡ ነግረውኝ ፡ እሱን ፡ ፍለጋ
ወደ ፡ ፍንክች ፡ ከተማ ፡ ከመጣሁ ፡ ለግንቦት ፡ ምሄል ፡ ነው ።
አሁን ፡ እሱም ፡ ሞታለች ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ሳይቆርጥ ፡ አይቀር
ምና ፡ ልፈልግ ፡ ብሎም ፡ አይነካ ። እኔም ፡ አላገኘው ፡ ባገኘ
ውስ ፡ እንዴት ፡ ላውቀው ፡ እችል ፡ ነበር ? እሱስ ፡ ምን ፡ ብሎ፡
ሊያስታውሰኝ ፡ ይችላል ? ኧረ ፡ ባክህን ፡ ተወኝ ! » አሉና ፡
አሁንም ፡ እሪ ፡ ማለትን ፡ ቀጠሉ ፤ እኔም ፡ የማጀብ ፡ ግዴታዬ ፡
ቀስቅሶኝ ፡ አብሬአቸው ፡ አለቅስኩና ፡ « በሉ ፡ እማሆይ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ከርሰዎ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፡ በዚች ፡ ዓለም ፡ የደረሰብ
ዎትን ፡ ድካም ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ያድርግ
ልዎት ፡ » ብዬ ፡ መርቄአቸው ፡ እኔም ፡ ልመናዬን ፡ እሳቸውም ፡

ጉዞአቸውን ፡ ቀጠልን ። እንግዲህ ፡ ያ ፡ የያሀ ፡ ቤተሰብ ፡ ታሪክ ፡ ውጤቱ ፡ ከዚህ ፡ ሊያልፍ ፡ አልቻለም ።

እማሆይ ፡ ወለተ ፡ ወልድ ፡ « ይህ ፡ ለማኝ ፡ ምነው ፡ አስለቀሰኝ ! የረሳሁትን ፡ አስታውሶ ፡ ስንቱን ፡ አስለፈለፈኝ ? ብቻ፡ እንኳንም ፡ ለፍልፌ ፡ ወጣልኝ ። የቸገረው ፡ ሰው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ስለሚያለቅስ ፡ አልቃሹ ፡ ሚች ፡ ዘመዱን ፡ በማስታወስ ፡ የሚያለቅስ ፡ መስሎ ፡ ይታየዋል ፡ ለተመልካች ፤ » በማለትና ፡ ምርኩዛቸውን ፡ ከእግሮቻቸው ፡ ጋር ፡ ተራ ፡ በማስገባት ፡ ወልገድ ፡ ወልገድ ፡ እያሉ ፡ ሲጓዙ ፡ ተቀምጬ ፡ እያለሁ ፡ ከዓይኖቼ፡ እስኪሰወሩ ፡ ሸኘኋቸው ።

እማሆይ፡«የልጅ ፡ ልጄ ፡ ተምሮአል ! ጥበበኛ ፡ ሆኖ ፡ መንግሥትም ፡ ወዶታል ! ከፍ ፡ ያለ ፡ እንጀራን ፡ አውጥቶአል» ፡ ብለው ፡ እርግጠኛ ፡ በመሆን ፡ ስንቱን ፡ በረሃ ፡ አቋርጠው ፡ ወደዚቹ ፡ ከተማ ፡ ከመጡ ፡ ይኸውና ፡ እንደነገሩኝ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ወራቸው ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ምነው ፡ « ከመጡ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እማን ፡ ዘንድ ፡ አረፉ ? ምንስ ፡ ይበላሉ ? » ብዬ ፡ ያልጠየቅኋቸው ? « እንዴ ! ብጠይቃቸውስ ፡ ምን ፡ ሊነግሩኝ ፡ ይችሉ ፡ ነበር ? በችግር ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ ቢደራረብ ፡ ችግሮች ፡ የተመሳሳይ ፡ ማግኔቶችን ፡ ጠባይ ፡ አይዙ ! ይህም ፡ ጠባይ ፡ ከሌለ ፡ የኔ ፡ ችግር ፡ ሊቃለል ፡ አይችል ! እረ ፡ እንኳን ፡ አልጠየቅኋቸው ፡ ባልጠይቃቸውስ ! ሁናቴአቸው ፡ ኑሮአቸውን ፡ ይገልጽ ፡ የለምን ? እማሆይ ! የድሮዋ ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ አያቴ ! እንደተበያየደ ፡ ብረት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ ይታይባቸው ፡ የለምን ? ይህ ፡ የጉስቁልና ፡ ኑሮ ፡ ውጤት ፡ መሆኑን ፡ አያስረዳምን ? አይ ፡ የኔ ፡ እማሆይ ፡ ተስፋ ! የልጃቸው ፡ ልጅ ፡ ለራሱ ፡ መቅኖ ፡ ያጣ ፡ መሆኑን ፡ ማን ፡ በነገራቸው ፤ ጥበበኛ ፡ ሆኖ ፡ መንግሥትም ፡ ወዶት ፡ በድሎት ፡ የሚኖርና ፡ እንጀራን ፡ ጠግቦ ፡ የሚበላ ፡ መስሏቸው ፡ ከራሱ ፡ ተርፎ ፡ ለእርሳቸውም ፡ እንዲጠቅም ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ በላይ ፡ ተጉዘው ፡



ለመጦር ፡ መጡልኛ ! ይህ ፡ ተስፋ ፡ ብቻ ፡ የአሥር ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ይጨምርላቸዋል ። » በማለት ፡ እየተደነቅኩና ፡ እማሆይን ፡ በአሳብ ፡ እያየኋቸው ፡ ከተቀመጥኩበት ፡ ሥፍራ ፡ ተነስቼ ፡ የኔ ፡ እማሆይ ፡ በተጓዙበት ፡ አቅጣጫ ፡ ጉዞዬን ፡ ቀጠልኩ ። አሳዛኝዋ ፡ እምዬ ፡ « በማሰብ ፡ ሰውነትህን ፡ አታስጨንቅ ፡» ያለችኝን ፡ በማስታወስ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ላለማሰብ ፡ ወስኜ ፡ መልክቴን ፡ በትያትር ፡ መልክ ፡ በመሞገት ፡ ለአንባቢዎች ፡ አቅርቤአለሁ ።